
# ተልዕኮአችን

መስከረም 2013| ቅጽ 5

## ከተሞችን በወንጌል መድረስ

**በዚህኛው ቅጽ ከተሞችን በወንጌል መድረስ በስፋት ይዳሰሳል**



# መልዕክት

ዘመንን ማለፍ ቀላል ያልሆ የእግዚአብሔር ምህረት እና ታላቅ ስጦታ የሆነ በረከት ነው። ዛሬ መስከረም 1, 2013 ዓ.ም ላይ ሆነን ዘመንን ለመሻገር እድል የሰጠንን እግዚአብሔርን እያመሰገንን ለመላው የተልዕኳችን ዲጅታል መጽሔይት አጋሮች እና አንባቢዎች በእራሴ እና በዚህ መጽሔይት ስራ ላይ እየተሳተ ባሉ ወንድም እና እህቶች ስም እንኳን ለ2013 በሰላም አደረሳችሁ ለማለት እወዳለሁ።

የተልዕኮአችን ዲጅታል መጽሄይት አምስተኛ ቅጽ እንድታነቡ፣ እንድትባረኩበት እና ለወንጌል ስራ እንድትነሳሱበት እነሆ በሚከተሉት የቴልግራም ቻናሎች ተለቋል። በዚህኛው ቅጽ ከተሞችን በወንጌል መድረስ በሰፊው የተዳሰሰበት ሲሆን የቤተክርስቲያን አገልግጋዮች፣ መሪዎች እና አማኒያን ሁሉ እንድታነቡት የአግልገሎት አቅታጫዎን እና በጽሑፎቹ የሚቀርቡ ምክሮችን እንድትጠቀሙ በጌታ ፍቅር እጠይቃለው።

መጽሔይቱን የምታገኙባቸው ቻናሎች

Mission talk with Aman (https://t.me/NationsforGod)
Naoel’s Perspective (https://t.me/NaolsP)
የቤሪያ ሰዎች በኢትዮጵያ (https://t.me/yeberiyasewoch)
መንፈሳዊ መጽሐፍት (https://t.me/amharicspritualbooks)

በተጨማሪም ጥያቄ እና አስተያየት ካልዎት
በስልክ ቁጥር ፡- +251920293652/ +251940094767 ይደውሉ
ኢ-ሜይል ፡- tsionamanuel9@gmail.com ያግኙን
አማኑኤል ገዛኸኝ



# ማውጫ


- ከተማ እና መጽሐፍቅዱሳዊ ምልከታዎች 1

- ከተሞችን ማዕከል ያደረገ ተልዕኮ በዚህ ዘመን በእድገት ላይ ያለው የከተሞች ጠቀሜታ 3

- የወንጌል ስርጭት እና የአዲስ አበባ ከተማ ጉዳይ 7

- ከተሞችና መልካም አጋጣሚዎቻቸው 9

- የከተማን የደም ሥሮች መረዳት ለወንጌል ተልዕኮ 13

- በየቀኑ 8 ክርስቲያኖች እየሱስን ለመከተል ባደረጉት ውሳኔ ይገደላሉ 15

- ወንጌላዊ ራይን ሃርድ ቦንኬ አ ፕ ሪ ል 1 9 4 0 - ዲ ሴምበ ር 2 0 19 16

- የአርጎባ ህዝብ ክፍል በኢትዮጽያ 22




# ከተማ እና መጸሐፍቅዱሳዊ ምልከታዎች

## ከተማ ምንድን ነው?

ዛሬ ከተማ የሚሰየመው የህዝብ ብዛትን ብቻ መሰረት በማድረግ ነው። በዛ ያለ ቁጥር ያለው ህዝብ የሰፈረበት ቦታ ከተማ፤ መለስተኛ ከሆነ ሰፈር አነስተኛ የሆነ ደግሞ መንደር የሚል ስያሜ ይሰጠዋል። ነገር ግን ይህንን ፍቺ መፅሀፍ ቅዱስ ላይ ልንጠቀመው አንችልም። በእብራይስጥ ቋንቋ 'ከተማ' የሚለው ቃል 'iyr' ሲሆን
ማንኛውንም የሰው ልጆች የሰፈሩበትን ቦታ ይገልፃል። አብዛኞቹ የጥንት ከተሞች ከ 1000 - 3000 የሚደርስ የህዝብ ቁጥር ነበራቸው። 'ከተማ' በመፅሀፍ ቅዱስ ውስጥ የህዝብ ብዛትን ከማመልከት ይልቅ ጥግግትን (Density) ያሳያል። መዝሙረ ዳዊት 122:3 ላይ ያለው ቃልም የዚህ ማሳያ ነው" .....እርስ በእርሷ እንደተገጠገጠች ከተማ....."። "ተገጠገጠች" የሚለው ቃል የተጠላለፈ ወይንም የተሳሰረ የሚል ትርጉም ይሰጠናል። በተመሸገች ከተማ ህዝቡ ይኖር የነበረው በተጠጋጉ ቤቶች እና መንገዶች ነበር። በርግጥ አብዛኞቹ የጥንት ከተሞች በግምት ከ 5 እስከ 10 Acre መሬት ላይ ያረፉ እና በአንድ Acre ወደ 240 ነዋሪዎችን የሚይዙ ነበሩ። በንፅፅር የኒውዮርክ ከተማ በአንድ Acre 105 ነዋሪዎችን ይይዛል።

በጥንት ጊዜ " ከተማ" የምንለው አሁን ላይ የተለያዩ አገልግሎቶችን በቅርበት ከምናገኝባቸውቦታዎች ጋር ይመሳሰላል። በጥግግት (Density) ምክንያት የመኖርያ እና የመስርያ ቤት፤ የመግዣ እና የመሸጫ፤ የመዝናኛ ቦታዎች እንዲሁም ማምለኪያ ቦታዎች የፍርድ ቤቶች ወዘተ ... ሁሉም በአንድ ቦታ ይገኛሉ። በጥንት ጊዜ የነበሩት ገጠራማ አካባቢዎች እና መንደሮች እነዚህን ሁሉ በአንድ ቦታ ሊያቀርቡ አይችሉም። ዛሬም ሰበርበን (SuBURB) የምንላቸው አካባቢዎች ከላይ የገለፅነውን አይነት አሰፋፈር አይከተሉም ይልቁንም አንድ አይነት እና ወጥ የሆኑ ግልጋሎቶችን ይሰጣሉ። ስለዚህም የመኖርያ፣ የመስርያ፣ የመጫወቻ እና የመማሪያ ስፍራዎች የተራራቁ ናቸው። ከአንዱ ወደ ሌላኛው ለመንቀሳቀስም ለመንገደኛ ምቹ ስላልሆነ መኪና ወይም ሌላ አማራጭ መጠቀም ያስፈልጋል።
አንድን ከተማ ከተማ ሚያስብለው የህይወት ስርዓቶችን ማቀራረቡ ነው። ሰዎችን ማለትም ነዋሪዎችን፣ የስራ ቦታዎችን ፣ ባህላዊ ተቋማትን ወዘተ ያቀራርባል። ገበያዎችን፣ የመንገድ ላይ ህይወቶችን፣ ሰዎች እርስ በእርስ እንዲገናኙም እድል ይፈጥራል። የመፅሀፍ ቅዱስ ፀሀፊዎች ከተማ ሲሉ ይህን አይነት ገፅታ ያለውን ቦታ ነው።

### የከተማ ተልእኮ በመፅሀፍ ቅዱስ

**እየሩሳሌም**

በብሉይ ኪዳን ቀደም ባሉት ጊዜያት እየሩሳሌም (የምድር ሁሉ ደስታ ) እንደ ከተማ ለእግዚአብሔር የማዳን እቅድ ወሳኝ የሆነችበት ምክንያት የሰው ህይወት በእግዚአብሔር ጌትነት ስር ሲገዛ ምን እንደሚመስል ለአለም ማሳያ ስለነበረች ነው። ብዙዎች በዚህ ጊዜ ስለነበረው ማእከላዊ የተልዕኮ ፍሰት ይናገራሉ። እግዚአብሔር አምላክ ያላመኑትን ህዝቦች ወደ ራሱ የሚስበው ክብሩን በሚገልጡ፤ ቅዱስ በሆኑ እና በኑሮአቸው የእርሱን ባህሪ በሚገልጡ በእስራኤል ህዝቦች በኩል ነበረ። (ዘዳግም4: 5-8) ነገር ግን በትንቢተ ዮናስ ላይ በአዲስ ኪዳን ሊመጣ ያለውን የተልዕኮ ፍሰት( የአማኞች ወደ አለም የመላክ) ለውጥ ቀድሞ አሳይቷል። ነብዩ ዮናስ ሰዎችን ወደ ንስሀ እንዲጠራ ወደ አላመኑ ህዝቦች የተላከ ብቸኛው የብሉይ ኪዳን ነብይ ነው። በትንቢተ ዮናስ በመጨረሻ የተፃፈው የጌታ ቃልም አስደናቂ ነው።

**ባቢሎን**

ከሳቢ ወደ ተስፋፊየተልዕኮ ለውጥ ወደ ሌላ ምእራፍ ያሸጋገረ ክስተት ተፈጥሮ ነበር። ይህም እስራኤላውያን ክፋት በሞላባት፣ ጣኦት በሚመለክባት እና ደም ወደምትጠማው ባቢሎን ተማርከው መወሰዳቸው ነው። "አማኞች በእንደዚህ አይነቱ ቦታ እንዴት መመላለስ ይገባቸዋል?" ለሚለው ጥያቄ ነብዩ ኤርምያስ በትንቢተ ኤርምያስ ምዕራፍ :28 ÷29 የአማኝ አቋም ምን መሆን እንዳለበት በጥሩ ሁኔታ አስቀምጧል። በትንቢተ ኤርምያስ 29:6 ላይ እግዚአብሔር አምላክ " ተባዙ ጥቂቶችም አትሁኑ በተጨማሪም በታላቋ ከተማ ባቢሎን ውስጥ ኑርል እንዲመሰርቱ እንዲሁም በከተማው ህይወት ውስጥ እንዲሳተፉ (ቤት እንዲሰሩ አትክልትም እንዲተክሉ ) ሲናገራቸው እናያለን። ከሁሉም በላይ ግን የከተማዋን " ሰላም እና ብልፅግና" እንዲፈልጉ " ስለእርስዋም ወደ እግዚአብሔር እንዲፀልዩ" ተነግሯችዋል። በከተማዋ ውስጥ የራሳቸውን ዘር እንዲያበዙ ብቻ ሳይሆን ባላቸው አቅም ለጋራ ጥቅም እንዲሰሩ ታዘዋል።
ይህ በጣም ሚዛናዊ ነው። የምድራዊ ከተማ እሴቶች ከእግዚብሔር ከተማ እሴቶች ጋር ጉልህ የሆነ ልዩነት ቢኖራቸውም የእግዚአብሔር ከተማ ዜጎች የምድራዊ ከተማቸው ምርጥ ዜጎች መሆን አለባቸው። እግዚአብሔር አይሁዶች ተማርከው በተወሰዱባት ከተማ ለጋራ ጥቅማቸው እንዲሰሩ አዟል። ይህም የራሱ የሆነ ግብ አለው። ምክንያቱም የከተማዋን ጥቅም መፈለግ እነርሱም እንዲሰፉ እና እንዲበለፅጉ ምርጡ መንገድ ነው። ትንቢተ ኤር 29:7 በዚህም ውስጥ የእግዚአብሔር ሀሳብ የማዳን እቅዱ ላይ እና ህዝቡን ማቋቋም ላይ ነው።

የቀጠለ....

አይሁዶችም የከተማውን ሰላም እና ጥቅም በመፈለጋቸው የሚያስፈልጋቸውን ተፅእኖ እና አቅም በማግኘት ወደ ሀገራቸው መመለስ ችለዋል። ከክርስቶስ መምጣት በኋላም በተለያዩ የአለም ክፍሎች ተበትነው የነበሩ አይሁዶች ለክርስትና መስፋፋት ወሳኝ ነበሩ።

## መጻተኛ ነዋሪዎች

እስራኤላውያን በምርኮ በነበሩበት ወቅት የነበራቸው ምልልስ አሁን ላለችው ቤተክርስትያን ምሳሌ መሆን ይችላልን? ለሚለው ጥያቄ መልሱ አዎ ነው። በምርኮ ጊዜ እስራኤል እንድ አለምአቀፍ ማህበረሰብ ተበትነው ይኖሩ ነበር እንጂ የሀገር ቅርፅ አልነበራትም። ይህ ደግሞ አሁን ያለችው ቤተክርስትያን ሁኔታ ጋር ያመሳስለዋል። ያእቆብ በ ያእቆብ መልእክት 1:1 ላይ "ለተበተኑት" ሲል ሀዋርያው ጴጥሮስ ደግሞ በ1ኛ የጴጥሮስ መልእክት 1:1 ላይ "መፃተኞች" በማለት ቤተ ክርስትያንን ገልፀዋታል። ሐዋርያው ጴጥሮስ " Parapidemois" የሚለውን ቃል እንግዳ ወይንም የአንድ ሀገር ተወላጅም ፤ነብኚም ያልሆነ ሰውን ለመግለፅ ሁለት ጊዜ ተጠቅሞበታል። ከዚህ በተጨማሪ አማኞች በማያምኑ ዘንድ በመልካም ስራ እና እግዚአብሔርን በማክበር እንዲመላለሱ እንዲሁም ስደት እና መከራም እንደሚኖር ተናግሯል።

(ወዳጆች ሆይ፥ ነፍስን ከሚዋጋ ሥጋዊ ምኞት ትርቁ ዘንድ እንግዶችና መጻተኞች እንደ መሆናችሁ እለምናችኋለሁ፤ ስለሚመለከቱት ስለ መልካም ሥራችሁ፥ ክፉ እንደምታደርጉ በዚያ እናንተን በሚያሙበት ነገር፥ በሚጎበኝበት ቀን እግዚአብሔርን ያከብሩት ዘንድ በአሕዛብ መካከል ኑሮአችሁ መልካም ይሁን።
1ኛ የጴጥሮስ መልእክት 2 : 11 - 12 )በትንቢተ ኤርምያስ ምእራፍ 29 ላይ ያለው እውነት ይህን ያረጋግጥልናል። አሁን ያሉ አማኞች ልክ እንደ አይሁድ ምርኮኞች የሚኖሩበትን ከተማ ጥቅም መፈለግ እንጂ ችላ ሊሉ አይገባም። በዙርያቸው ያለው ማህበረሰብ በኑሮአቸው እና በአገልግሎታቸው ሊሳቡም ሆነ ሊያስቆጡ እንደሚችሉ ማወቅ አለባቸው። አንዳንዶችም መልካም ስራቸውን አይተው እግዚያብሔርን ያከብራሉ።

ሚሮስላቭ ቮልፍ 1ኛው የጴጥሮስ መልእክት ላይ ተመስርቶ በፃፈው "Soft difference" በተሰኘው ፅሁፍ ላይ ሀዋርያው በመልእክቱ ያንፀባረቀው ውጥረት እስካሁን ከነበሩት ክርስቶስን ከባህልን የማዛመድ ምሳሌዎች ጋር እንደማይዛመዱ ገልጾዋል።
ሐዋርያው ጴጥሮስ አለም ወንጌልን ሙሉ ለሙሉ ሊቀበለው እንዳማይችል እና ብዙዎችን ደግሞ እንደማያስደስት ተናግሯል። ይህ ደግሞ የባህል ለውጥን ለማምጣት እና በቤተክርስቲያን እና በመንግስት መሀከል ትብብር ከመፍጠር እሳቤ ጋር ይጋጫል።

ይህን እሳቤ ለሚከትሉ አማኞችም ማስጠንቀቂያ ነው። ይህን እሳቤ ለሚከተሉ የወንጌል አማኞችም ቀይ በተመሳሳይ በሌላ ጥግ ላይ ያለው ክርስትና በባህል ላይ ምንም አይነት ተፅእኖ አይኖረውም ለሚለው እሳቤ 1ኛ ጴጥሮስ 2:12 እና ማቴዎስ 5:16 ላይ ያሉት ቃሎች ክርስትና ብዙዎችን መማረክ እንደሚችል እና ሰዎች እግዚአብሔርን እንዲያከብሩ እና እንዲያመሰግኑ የማድረግ አቅም እንዳለው ያሳያሉ።

## ሰማርያ እና የምድር ዳርቻ

አሁን ያለችው ቤተ ክርስትያን እስራኤል በምርኮ ጊዜ በነበረችበት ሁኔታ በአለም በሁሉም ቦታ ተበትና ትገኛለች። በ ሐዋርያት ስራ 8 ላይ ጌታ ክርስትያኖች ከኢየሩሳሌም ውጪ በየቦታው እንዲበተኑ አድርጓል። ይህም የወንጌል ስፍራ እንዲሰፋ ምክንያት ሆኗል። ወድያውም በጊዜው የነበሩ ክርስትያኖች አይሁዶች ይፀየፏት ወደ ነበረችው ሰማርያ አቅንተው ነበር። ነገር ግን እንደ ነብዩ ዮናስ እና የአይሁድ ምርኮኞች ምንም ሳያንገራግሩ በወንጌል የተቀየሩት ክርስትያኖች በሰማርያን በከተማ የወንጌል ተልዕኮ ተሰማርተዋል።

በመጀመርያዋ ቤተክርስትያን እንደቀደመው ጊዜ አንድን ከተማ ማእከል ያደርገ የተልእኮ ፍሰት አልነበረም። ይልቁንም ሁሉም የአለም ከተሞች ወሳኝ ነበሩ። በሐዋርያት ስራ ምእራፍ
17 ላይ የእውቀት ማዕከል ወደ ሆነችው አቴንስ፤ በምእራፍ 19 በጣኦት አምልኮ ወደምትታወቀው ኤፌሶን፤ በመጨረሻም የፓለቲካ እና የወታደራዊ ሀይል ማእከል ወደሆነቸው ሮም አቅንቷል። ጆን ስቶት የተባለ ሰው " ጳውሎስ ከአንዱ እስትራቴጂክ ከተማ ወደ ቀጣዩ የመጓዝ የራሱ የሆነ መመርያ ያለው ይመስላል።" ሲል ተናግሯል። ከተማውን በወንጌል በመድረስ መላ ማህበረሰቡን በወንጌል እንዲደርስ አስችሎታል ለዚህም የቆላስያስ ደብዳቤ ማረጋገጫ ነው። በዚህ መልእክቱ ላይ ጳውሎስ በሎዶቅያ፣ በኢያራ እና ሌሎች በአካል ባልሰበከባቸው ቦታዎች የሚኖሩ (ምናልባትም በኤፌሶኑ አገልግሎት ወደ እምነት የመጡ) ደቀመዝሙራትን ይከታተል እንደነበር እናያለን። ወንጌል በከተማው ማእከል ከተሰበከ በዙርያው ያሉ ቦታዎች እና ማህበረሰቦችን መድረስ ይቻላል።
ከተማን ማዕከል ያደረጉ የወንጌል እንቅስቃሴዎች ውጤታማ የሆኑበት ምክኒያቶችን እንደሚኬለው ጠቅለል
አድርገን ልንገልጽ እንችላለን፦

· ከተሞች ከባህል አንጻር በጣም ቁልፍ ናቸው።
· ከተሞች ከአለም አቀፍ ነባራዊ ሂሁኔተራዎች አንጻር ቁልፍ ናቸው።
· ከተሞች በግለሰብ ደረጃ ትልቅ ቦታ የሚሰጣቸው ቦታዎች ባቸው

የመጀመሪያዋ ቤተክርስቲያን በአብዛኛው የከተማዎች ውስጥ እንቅስቃሴ ነበረች በዚህም አብዛኛውን የሮም ከተማ ማዳረስ የቻሉ ሲሆን የተቀሩት የክፍለ ሃገራት ክፍሎች ግን በአብዛኛው ያልተደረሱ ሆነው ቆይተዋል።

ወደ ገጽ 4 ዞሯል...

# ከተሞችን ማዕከል ያደረገ ተልዕኮ
# በዚህ ዘመን
# በእድገት ላይ ያለው የከተሞች ጠቀሜታ

በ1950 ከ10 ሚሊየን  ህዝብ  በላይ ያላቸው ከተሞች ለንደን እና አሜሪካ ብቻ ነበሩ። በአሁኑ ጊዜ ግን ተመሳሳይ ገጽታ ያላቸው ከ 20 በላይ ከተሞች ይገኛሉ ::በነዚህ ሁለት አስርት አመታት ውስጥ 12ቱ ከፍተኛውን ደረጃ ይዘዋል ። 10 እና ከዚያ በላይ ወደዚህ  እድገት ሊጨመሩ ያሉ አሉ። የአለም ከተማዎች በባህላዊ እና ኢኮኖሚያዊ እሴቶች ጠንካራ እየሆኑ ይገኛሉ። ከተሞች የአለማቀፋዊ፣ ማህበራዊና ቴክኖሎጃዊ መረቦች መቀመጫ ማዕከል ናቸው ። የቴክኖሎጂ እና መገናኛ አብዮት ማለት የአለም አቀፋዊ ከተሞች ባህል እና እሴቶች ወደ እያንዳንዱ ጎሳ እና ህዝብ መሰራጨት ነው። በሎዋ እንዲሁም  በሜክሲኮ ያሉ ህጻናት በራሳቸው አካባቢ ካሉ አዋቂዎች በላይ በሎሳንጀለስና በኒውዮርክ ያሉትን ታዳጊዎች እና ጎልማሶችን እየመሰሉ ይገኛሉ። ሊመጣ ያለው ስርዓት አለምአቀፋዊ፣ብሄርብሄረሰባዊ እና ከተማ ቀመስ ስርዓት ነው።

የአለም ከተማዎች የባህልና ህይወትን ድባብ ለማስፈን ወሳኝ ሚና እየተጫወቱ ነው። እንደ አውሮፓ እና ሰሜን አሜሪካ ያሉ ቦታዎች ራሱ በመጠን እያደጉ አይደለም። የአለም ከተሞችን ለክርስቲያናዊ  ተልዕኮ ጠቃሚ የሚያደርጋቸው ሁለተኛ ምክንያትም አለ። በሚሊዮኖች የሚቆጠሩ ወደ ከተሞች የሚፈልሱ ሠዎች ለክርስትና እምነት በፊት ከነበሩት በላይ ክፍት እንዲሆኑ የሚያደርግ ፀባይ አላቸው። በመጀመሪያ ደረጃ ለአዲስ ሀሳቦች ክፍት ናቸው።በባህላዊ ድባብ ውስጥ ቆይተው ስለሚመጡ በአጠቃላይ ለለውጥ ክፍት ናቸው ።በሁለተኛ ደረጃ የከተማ ህይወት በሚያሳድረው መንፈሳዊ ፣ኢኮኖሚያዊ ፣ሞራላዊ ተፅህኖ ድጋፍና እርዳታ ይፈልጋሉ። ድሮ በክፍለሀገር የነበረው የድጋፍ ትስስር ደካማ ነው ወይም ከነጭራሹ የለም ፣ በእድገት ላይ ያለው አለም  ደግሞ "ከመንግስት አገልግሎት ቀጥሎ " በሌላ በኩል ቤተክርስቲያን ድጋፍ ማህበረሰብ ያዘጋጃል፣ አዲስ የመንፈሳዊ ቤተሰብ፣እርነት የሚያወጣ የወንጌል መልዕክት "እነዚህን አዲስ የከተማ ነዋሪዎች ፍላጎቶች ሊያሟሉ የበለጸጉ ምርጥ ቡድኖች ይጠብቋቸዋል ፣ሠውነትንናነፍስን መመገብ የሚችሉ ናቸው።

የአውዳዊ ቤተክርስቲያን አስፈላጊነት
ይሁንና በከተማ ተልዕኮ ላይ ከፍተኛ ተጽዕኖ ያሳድራል፤ ከተማው ራሱ ወይም የመኖሪያ ቦታው ሳይሆን ቤተክርስቲያን ነው። የብዙ ወንጌላውያን አብያተ ክርስቲያናት ስሜት ፀረ ከተማዊነት ነው። ብዙ አገልግሎቶች የሚቀረፁት ከከተማ ውጪ ነው። በመቀጠል በከተማ ነዋሪዎችና በወንጌል ላይ ያለውን መሰናክል ከግምት ባለማስገባት በቀላሉ ወደ ከተማ ይገባል። እንደዚህ አይነት አገልጋዮች ወደ ከተማ መጥተው አገልግሎት ሲጀምሩ ወንጌልን ለመስበክና የከተማውን ህዝብ ለማሸነፍ ይከብዳቸዋል። ልክ መፅሐፍ ቅዱስ በአንባቢው አነጋገር እንደሚተረጎመው ነዋሪ በሚረዳው መልኩ ሊገለፅ እና ሊገናኝ ይገባዋል። የትኞቹ የቤተክርስቲያን ባህሪያት አውዳዊና ከተማ በቀል ናቸው።
በከተማ ተልዕኮ አገልግሎት ውስጥ ያሉ ሠዎች በጎሣና ማህበራዊ ኢኮኖሚያዊ ደረጃዎች መሀል ስላሉት ልዩነቶች ግንዛቤ ያላቸው ቢሆን፤  ተመሳሳይነት ባለው አካባቢ  የሚኖሩ ሠዎች ግን የራሳቸው ልምዶችና አስተሳሰቦች ለራሳቸው መደብና ዘር ብቻ የሚሆኑ እንደሆኑ ማስተዋል ሲቸገሩ እንመለከታለን። በአጭሩ ውጤታማ የከተማ ቤተክርስቲያን መሪ ስለ ጎሳ፣ መደብ፣ ዘርና ሀይማኖት ልዩነቶች የመረዳት ችሎታ ከፍተኛ ግንዛቤና እውቀት ያለው ሊሆን ያስፈልጋል ። በከተማ የሚኖሩ ከሁለት የተለያየ ዘር የመጡ ሠዎች ሁለት የተለያዩ ነገሮችን በማመልከት አንድ ቃል ሊጠቀሙ ይችላሉ ። ስለዚህ የዘር ቡድኖች ጉዳይ ሲቀርቡ በልዩነት እና ጥንቃቄ በተሞላበት መልኩ ነው።
ሁለተኛ ባህላዊ ወንጌላውያን አማኞች ከቤተክርስቲያን ቅጥር ግቢ ውጪ ከትምህርት፣ ስራ፣ ጥበብ፣ ገቢ የህዝብ አቋምና መንግስት ጎን ለጎን የክርስትና እምነታቸውን እንዴት መለማመድ እንዳለባቸው መረዳት ላይ እምብዛም ናቸው። ከከተማ ውጪ ህይወትን ከፋፍሎ መኖር ይቻል ። በከተማዎች ግን ይህን ማድረግ አይቻልም ምክንያቱም ሠዎች የሚኖሩት በስራቸው ውስጥ ረጅም ጊዜ በማሳለፍ ነው።
ሶስተኛ የአብዛኛው የወንጌላውያን ቤተክርስቲያን የስራ ባህል መካከለኛ ደረጃ የሚገኙ ናቸው። ሰዎች ለግል ህይወት ነጻነታቸውን፣ የደህንነታቸው መጠበቅ፣ ግልጽነትና ለስርአት ትልቅ ዋጋ ይሰጣሉ። በሌላ በኩል ደግሞ ከተማ በምፀት ፣ በቁጣ ናልዩነት ወዳድ ረብሻና አሻሚነትን በሚሹ ሰዎች የተሞላ ነው። የቤተክርስቲያን አገልጋዮች በከተማው ባህል መሠረት መስራት ሳይችሉ ሌላ ከተማዊ ያልሆነ የተልዕኮ አካባቢ ለመመስረት ከሞከሩ ጎረቤቶቻቸውን መድረስ መለወጥና ማዋሀድ እንደማይችሉ ይረዳሉ።

ከገጽ 2 የቀጠለ....

አይሁዶችም የከተማውን ሰላም እና ጥቅም በመፈለጋቸው የሚያስፈልጋቸውን ተፅእኖ እና አቅም በማግኘት ወደ ሀገራቸው መመለስ ችለዋል። ከክርስቶስ መምጣት በኋላም በተለያዩ የአለም ክፍሎች ተበትነው የነበሩ አይሁዶች ለክርስትና መስፋፋት ወሳኝ ነበሩ።

## መጻተኛ ነዋሪዎች

እስራኤላውያን በምርኮ በነበሩበት ወቅት የነበራቸው ምልልስ አሁን ላለችው ቤተክርስትያን ምሳሌ መሆን ይችላልን? ለሚለው ጥያቄ መልሱ አዎ ነው። በምርኮ ጊዜ እስራኤል እንድ አለምአቀፍ ማህበረሰብ ተበትነው ይኖሩ ነበር እንጂ የሀገር ቅርፅ አልነበራትም። ይህ ደግሞ አሁን ያለችው ቤተክርስትያን ሁኔታ ጋር ያመሳስለዋል። ያእቆብ በ ያእቆብ መልእክት 1:1 ላይ "ለተበተኑት" ሲል ሀዋርያው ጴጥሮስ ደግሞ በ1ኛ የጴጥሮስ መልእክት 1:1 ላይ "መፃተኞች" በማለት ቤተ ክርስትያንን ገልፀዋታል። ሐዋርያው ጴጥሮስ " Parapidemois" የሚለውን
ቃል እንግዳ ወይንም የአንድ ሀገር ተወላጅም ፤ጎብኚም ያልሆነ ሰውን ለመግለፅ ሁለት ጊዜ ተጠቅሞበታል። ከዚህ በተጨማሪ አማኞች በማያምኑ ዘንድ በመልካም ስራ እና እግዚአብሔርን በማክበር እንዲመላለሱ እንዲሁም ስደት እና መከራም እንደሚኖር ተናግሯል።

(ወዳጆች ሆይ፥ ነፍስን ከሚዋጋ ሥጋዊ ምኞት ትርቁ ዘንድ እንግዶችና መጻተኞች እንደ መሆናችሁ እለምናችኋለሁ፤ ስለሚመለከቱት ስለ መልካም ሥራችሁ፥ ክፉ እንደምታደርጉ በዚያ እናንተን በሚያሙበት ነገር፥ በሚጎበኝበት ቀን እግዚአብሔርን ያከብሩት ዘንድ በአሕዛብ መካከል ኑሮአችሁ መልካም ይሁን።
1ኛ የጴጥሮስ መልእክት 2 : 11 - 12 )በትንቢተ ኤርምያስ ምእራፍ 29 ላይ ያለው እውነት ይህን ያረጋግጥልናል። አሁን ያሉ አማኞች ልክ እንደ አይሁድ ምርኮኞች የሚኖሩበትን ከተማ ጥቅም መፈለግ እንጂ ችላ ሊሉ አይገባም። በዙርያቸው ያለው ማህበረሰብ በኑሮአቸው እና በአገልግሎታቸው ሊሳቡም ሆነ ሊያስቆጡ እንደሚችሉ ማወቅ አለባቸው። አንዳንዶችም መልካም ስራቸውን አይተው እግዚያብሔርን ያከብራሉ።

ሚሮስላቭ ቮልፍ 1ኛው የጴጥሮስ መልእክት ላይ ተመስርቶ በፃፈው "Soft difference" በተሰኘው ፅሁፍ ላይ ሀዋርያው በመልእክቱ ያንፀባረቀው ውጥረት እስካሁን ከነበሩት ክርስቶስን ከባህልን የማዛመድ ምሳሌዎች ጋር እንደማይዛመዱ ገልጾዋል።
ሐዋርያው ጴጥሮስ አለም ወንጌልን ሙሉ ለሙሉ ሊቀበለው እንዳማይችል እና ብዙዎችን ደግሞ እንደማያስደስት ተናግሯል። ይህ ደግሞ የባህል ለውጥን ለማምጣት እና በቤተክርስቲያን እና በመንግስት መሀከል ትብብር ከመፍጠር እሳቤ ጋር ይጋጫል።

ይህን እሳቤ ለሚከትሉ አማኞችም ማስጠንቀቂያ ነው። ይህን እሳቤ ለሚከተሉ የወንጌል አማኞችም ቀይ በተመሳሳይ በሌላ ጥግ ላይ ያለው ክርስትና በባህል ላይ ምንም አይነት ተፅእኖ አይኖረውም ለሚለው እሳቤ 1ኛ ጴጥሮስ 2:12 እና ማቴዎስ 5:16 ላይ ያሉት ቃሎች ክርስትና ብዙዎችን መማረክ እንደሚችል እና ሰዎች እግዚአብሔርን እንዲያከብሩ እና እንዲያመሰግኑ የማድረግ አቅም እንዳለው ያሳያሉ።

## ሰማርያ እና የምድር ዳርቻ

አሁን ያለችው ቤተ ክርስትያን እስራኤል በምርኮ ጊዜ በነበረችበት ሁኔታ በአለም በሁሉም ቦታ ተበትና ትገኛለች። በ ሐዋርያት ስራ 8 ላይ ጌታ ክርስትያኖች ከኢየሩሳሌም ውጪ በየቦታው እንዲበተኑ አድርጓል። ይህም የወንጌል ስፍራ እንዲሰፋ ምክንያት ሆኗል። ወድያውም በጊዜው የነበሩ ክርስትያኖች አይሁዶች ይፀየፏት ወደ ነበረችው ሰማርያ አቅንተው ነበር። ነገር ግን እንደ ነብዩ ዮናስ እና የአይሁድ ምርኮኞች ምንም ሳያንገራግሩ በወንጌል የተቀየሩት ክርስትያኖች በሰማርያን በከተማ የወንጌል ተልዕኮ ተሰማርተዋል።

በመጀመርያዋ ቤተክርስትያን እንደቀደመው ጊዜ አንድን ከተማ ማእከል ያደርገ የተልእኮ ፍሰት አልነበረም። ይልቁንም ሁሉም የአለም ከተሞች ወሳኝ ነበሩ። በሐዋርያት ስራ ምእራፍ
17 ላይ የእውቀት ማዕከል ወደ ሆነችው አቴንስ፤ በምእራፍ 19 በጣኦት አምልኮ ወደምትታወቀው ኤፌሶን፤ በመጨረሻም የፓለቲካ እና የወታደራዊ ሀይል ማእከል ወደሆነቸው ሮም አቅንቷል። ጆን ስቶት የተባለ ሰው " ጳውሎስ ከአንዱ እስትራቴጂክ ከተማ ወደ ቀጣዩ የመጓዝ የራሱ የሆነ መመርያ ያለው ይመስላል።" ሲል ተናግሯል። ከተማውን በወንጌል በመድረስ መላ ማህበረሰቡን በወንጌል እንዲደርስ አስችሎታል ለዚህም የቆላስያስ ደብዳቤ ማረጋገጫ ነው። በዚህ መልእክቱ ላይ ጳውሎስ በሎዶቅያ፣ በኢያራ እና ሌሎች በአካል ባልሰበከባቸው ቦታዎች የሚኖሩ (ምናልባትም በኤፌሶኑ አገልግሎት ወደ እምነት የመጡ) ደቀመዝሙራትን ይከታተል እንደነበር እናያለን። ወንጌል በከተማው ማእከል ከተሰበከ በዙርያው ያሉ ቦታዎች እና ማህበረሰቦችን መድረስ ይቻላል።
ከተማን ማዕከል ያደረጉ የወንጌል እንቅስቃሴዎች ውጤታማ የሆኑበት ምክኒያቶችን እንደሚኬለው ጠቅለል
አድርገን ልንገልጽ እንችላለን፦

- ከተሞች ከባህል አንጻር በጣም ቁልፍ ናቸው።
- ከተሞች ከአለም አቀፍ ነባራዊ ሂሁኔተራዎች አንጻር ቁልፍ ናቸው።
- ከተሞች በግለሰብ ደረጃ ትልቅ ቦታ የሚሰጣቸው ቦታዎች ባቸው

የመጀመሪያዋ ቤተክርስቲያን በአብዛኛው የከተማዎች ውስጥ እንቅስቃሴ ነበረች በዚህም አብዛኛውን የሮም ከተማ ማዳረስ የቻሉ ሲሆን የተቀሩት የክፍለ ሃገራት ክፍሎች ግን በአብዘኛው ያልተደረሱ ሆነው ቆይተዋል።
ይሁንና ክርስትና አብዛውን የከተማ ክፍል መድረስ የቻለ ስለነበር በግዜ ሂደት
ያልተደረሱ የነብትን የክፈለ ሃገራት መድረስ ችሎ ነበር፤ የክርስትና ከፍታ በሚል ራውድኒ ስታርክ ይህን አሳብ ታካፍለናለች ።
የክርስቲያንየወንጌል ተልዕኮ የግሪኮ -ሮማን ጥንታዊ ስልጣኔ መውረስ የቻለው ከተሞችን መውረስ ስለቻለም ነው።

ምንጭ፡ ሉዛን ሙቭመንት, 2010
ትርጉም፡- ቤዛዊት በቀለ

ከገጽ 4 የቀጠለ....

## ከተሞችን ማዕከል ያደረገ ተልዕኮ በዚህ ዘመን
## በእድገት ላይ ያለው የከተሞች ጠቀሜታ

አራተኛ ከተማ ያልሆኑ ቤተክርስቲያኖች ተቋቁመው ሊቆዩ የሚችሉት ከፍተኛ የማህበራዊ ዝምድና ወይም ያልተሰበረ ትስስር ባለበት ቦታ ነው። የከተማ ጉርብትና ከሌሎች አይነቶች እጅግ የተወሳሰበ ነው እና ደግሞ ቤተክርስቲያኖች ጉርብትናቸውን ለወንጌል ብቻ ማድረግ አይችሉም። ምንም እንኳን ከግቦቹ አንዱ ቢሆን እንኳ ።ለጤናማና ጤናማ ጉርብትና መንገድ ይፈልጋሉ ።ለከተማው ደህንነት ያስባሉ ፣።የኤርምያስ 29 መንፈስ።

ጥንታዊ ለዘብተኛ ሚባሉ ቤተክርስቲያኖች ተልዕኮን ከማህበራዊ ለውጥ ጋር ብቻ ያያይዙታል። ግባቸው ከተማዋን ፍትሃዊና ሰብዓዊ ማድረግ ነው ፣ ለጋራ ጥቅም ኢኮኖሚያዊና ሰብአዊ ጥቅም መስራት ነው። ይሄ በከፊሉ ልክ ነው። በጥንቱ ወግ የፀናችው ቤተክርስቲያን እድገት ጋር ብቻ ታያይዘዋለች። ግቡ የሚሆነው በከተማ ውስጥ የክርስቶስን ቤተክርስቲያን በማሳደግ ለእግዚአብሔር የሚድኑ እና ወደ መንግስቱ መጨምር ሲሆን ከዚህ ባለፈ የቤተክርስቲያንን፣ አቅም ማሳደግ ነው ። ቢሆንም እነዚህ ሁለት ነገሮች መዋሀድ መቻል አለባቸው ምክንያቱም ሁለቱም ለብቻቸው አቅም ሊያጡ ይችላሉ። የከተማን ህይወት ሁለቱም ተቋቁመው መቆየት አይችሉም። ስለዚህ የሚድኑ ሰዎች ጸንተው የሚቆሙበት የተለወጠ፣ ፀጋና ሀይል የተሞላ አዲስ ውልደት ያስፈልጋል። በሌላ በኩል ቤተክርስቲያን የጎረቤቶቻቸዉን የጋራ ጥቅም ችላ በሚሉ ወይም በሚጠሉ ሰዎች ከተሞላች በሚሰቀጥጥ ሁኔታ እንቅስቃሴዎቿ ሁሉ ይሞታሉ።

ለሁሉም ሳይሆን ለቤተዕምነቱ ሰዎች ብቻ መልካምን የምታደርግ ቤተክርስቲያን (ገላትያ 6:10) በትክክል እንደ ብሄርተኛና ወገንተኛ ትታያለች። ሀይማኖት የለሽ ሰዎች መልካም ስራህን ካላዩ እግዚአብሔርን አያከብሩም። በሌላ አባባል ቤተክርስቲያናት ሀይላቸዉን ሁሉ ወንጌል መስበክ ላይ አውለው ከተማይቱ ማገልገል ላይ ምንም ጉልበት ባያወጡ የወንጌል አገልግሎታቸው ውጤታማ አይሆንም። ፀጋን መለማመድ በማያጠራጥር መልኩ እርዳታ እና የኛን መዘርጋት እና መሰጠት ለሚያስፈልጋቸው ሰዎች ወደ መስጠት ህይወት ይመራል። (የኢሳ 1÷10-18፣ 58÷1-10፣ ያዕ 2÷14-17)እስራኤላውያን ድሀ ማገልገል እንዳለባቸው እግዚአብሔር ይናገራል። ምክንያቱም እነሱም በግብፅ እያሉ ምፃተኞች ነበሩና (ዘዳ 10:19) ፀጋን መለማመድ ሁልጊዜም ለድሀውና ለማያምነው ጎረቤታችን ፍቅርን ወደማሳየት ይመራናል።

በመፅሀፍ ቅዱስ መሰረት ወንጌልን በመስበክ ሰዎችን ለደህንነት የመጋበዝ አገልግሎት ያለንንወደ ማካፈልና የተቸገሩትን ወደመርዳት ይመራል እና አለም ይህንን መረዳዳት ሲያዩ"በእነሱ መሀል የተቸገረ እንዳልነበረ ሲያዩ( ሐዋ 4:34) ሀይል ወዳለው የወንጌል ምስክርነት ይመራል ።

ከተማን ለመድረስ ንቅናቄ ያስፈልጋል

አንድን ከተማ ሙሉ በሙሉ በወንጌል መድረስ ከፍተኛ መንፈሳዊ ተሐድሶና አዲስ አቅጣጫ ላይ የሚገኙ ብቁ እና ፍቱን አብያተክርስትያናትን ከማቀፍ የዘለለ ተግባርን ይፈልጋል። ከተማን በወንጌል ለመለወጥ ራስን ቀጣይ በሆነ መልኩ ማበልጸግን፣ የመንፈሳዊ አገልግሎቶች ተፈጥሮአዊ የእድገት እንቅስቃሴ እና አዲስ በሚተከሉ አብያተክርስቲያናት ማዕከል ዙሪያ የመኖር የግንኙነት መረብን ይጠይቃል።

ይህ ምንን ይመስላል?

አማኞች በከተማ ውስጥ በአገልጋይነት አመለካከት ይኖራሉ። አዳዲስ የንግድ ተቋማትና ለትርፍ ያልተቋቋሙ ድርጅቶች በትልቅም ሆነ በትንሽ መንገድ በማሕበረሰቡ ውስጥ ያላቸውን ባሕል ያሳድጋሉ። አማኞች እምነታቸውን ከስራቸው ጋር ያጣምራሉ በዚህም ምክንያት እያንዳንዱ

ጥሪ የመንግስቱ ስራ ይሆናል። የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት መንፈሳዊ አገልግሎቶችና ሌሎች ወንጌል ተኮር ተቋማት በከተማ ውስጥም ሆነ ወደ አጥቢያ ቤተክርስቲያናት የሚሄዱ አማኝ መሪዎችን ያሳድጋሉ። ሰዎች በማሕበረሰብ ማዕቀፍ ውስጥ ያላቸውን ሀብት፣ ስልጣንና ተጽዕኖ የመፍጠር አቅማቸውን መንፈሳዊ አገልግሎቶችን ለማበልጸግ እና አዳዲስ አብያተክርስቲያናትን በመትከል ለሌሎች ጥቅም ያውላሉ። አብያተ ክርስቲያናት እና አማኞች የጥበብ ስራዎችን ይደግፋሉ ይሰራሉም። እስቲ እነዚህን በዝርዝር እንመልከት።

1. አዳዲስ አብያተክርስቲያናት ስነምህዳር ከወንጌል አንጻር እነዚህ አጥቢያ አብያተ ክርስቲያናት ንጹሕ መንፈሳዊ አየርን በማሕበረሰቡ ውስጥ በማሰራጨት የአማኞችን ግንኙነትና ከተማን የማደስና የመዋጀት እጅግ ከባድ ስራን ያግዛሉ። እነዚህ አጥቢያ ቤተክርስቲያናት ቀዳሚ ደቀመዝሙር አድራጊ እና አማኞችን የማብዛት ስራን የሚሰሩ እንዲሁም በአዲስ አሳብ ለሚነሱ አገልግሎቶች የፋይናንስ ምንጭ ናቸው። ይህ ሥነምህዳር የአብያተ ክርስቲያናትና የአዲስ አብያተክርስቲያናት መገኛ ነው። አብያተክርስቲያነቱ ወንጌልን መዕከል ያደረጉ፣ ከተማ አቀፍ፣ ተልዕኳዊ/ ወንገላውያን፣ ሚዛናዊ፣ አዳጊ እና ምሳሌያዊ መሆን ይጠበቅባቸዋል። ይህ እጅግ መሰረታዊ ሥነምህዳር ነው።

2. ይህ ስነምህዳር የተመረጡ ሕዝቦችን የሚደርሱ የወንጌላውያንን ስርዓትና የግንኙነት መረብ ያሳድጋል። አዲስ መሪዎችን በመፍጠር ሂደት ላይ እጅግ አስፈላጊ እንቀሳቃሽ ከሆኑት የከፍተኛ ትምሕርተ ተቋማት ከመንፈሳዊ አገልግሎቶች በተጨማሪ፤ በአንድ የስራ መስክ ላይ ትኩረት አድርገው የሚሰሩ በወንጌል አማኞች ተቋማት ከፍተኛ የማሕበረሰብ ክፍሎችን፣ ደሃዎችን፣ ሙስሊሞችን፣ ሂንዱዎችን እና ሌሎች ልዩ የባሕልና የኃይማኖት ክፍሎችን ለመድረስ እጅግ አስፈላጊ ናቸው።

የቀጠለ....

## ከተሞችን ማዕከል ያደረገ ተልዕኮ በዚህ ዘመን
## በእድገት ላይ ያለው የከተሞች ጠቀሜታ

3. በመደበኛ ስራ ላይ የሚገኙ የማሕበረሰብ መሪዎች የግንኙነት መረብና ተቋማት
ለምሳሌ ያህል የንግድ፣ የመንግስታዊ፣ የትምሕርት፣ የመገናኛ ብዙኃን እና የሥነ ጥበብ ተቋማት የሥነምህዳሩ አካል ናቸው። በእነዚህ ተቋማት ውስጥ የሚገኙ ግለሰቦች በቤተክርስቲያን ውስጥ መኖር ደቀመዝሙር የሆኑ ግለሰቦችን ለማህበራዊው ሕይወት ለመደገፍ እጅግ አስፈላጊ ነው። እነዚህ ግለሰቦች በመደበኛ የስራ መስኮች ላይ፣ ባሕላዊ ድርጅቶችና ትምሕርቶችን ማዘጋጀት ላይ በመደጋገፍ እና እርስ በእርስ ህብረት ማድረግ ይኖርባቸዋል።

4. ይህ ስነምህዳር በከተማዎች ወስጥ ሰላምን የሚሰብኩ አማኞችን በሚያፈሩ ድርጅቶችና ፕሮጀክቶች ውስጥ በግልጽ የሚታይ ነው።
በከተማዎች ውስጥ የሚገኙ በመቶዎችና በሺህዎች የሚቆጠሩ ንግዶችና ለትርፍ ያልተቋቋሙ ድርጅቶች ለሁሉም የማሕበረሰብ ክፍል ሰላም ለማስፈን የበኩላቸውን መወጣት እና የተቸገሩትን መርዳት ላይ ትኩረት ማድረግ ይጠበቅባቸዋል። የተባበረ እና የተቀናጀ የጥምር አብያተክርስቲያናት ተቋማት መኖር አማኞችን በግለሰብና በቤተሰብ በቀጣይ በከተማ በሚኖራቸው ኑሮ ውስጥ ድጋፍ ያደርጉላቸዋል (ለምሳሌ፡ - ትምሕርት ቤቶች፣ የስነ መለኮት ኮሌጆች፣ ሌሎች መሰል አማኞችን በከተማው ውስጥ የሚያግዙ
ተቋማት)

5. በተጨማሪም ይህ ሥነምህዳር በከተማው በሚገኙ መሪዎች መካከል ተደራራቢ አይነት መልክ አለው።
የቤተክርስቲያን እንቅስቃሴ መሪዎች፣ የስነ-መለኮት ምሁራን፣ አስተማሪዎች፣ የተቋማት ኃላፊዎች እና የማህበረሰብ መሪዎች በሚኖራቸው ተጽዕኖ የማሳደር አቅምና ሀብት እርስ በእርሳቸው አልፎም ለመላ ከተማው የሚሆን ራዕይና አቅጣጫ ያዘጋጃሉ።
የከፍታ ጣሪያ:-እነዚህ የተለያዩ ድርጊቶች ወይም ግለሰባዊ ዕደገቶች ቀጣይነት ባለው መንፈሳዊ እንቅስቃሴ ጋር በመድረስ ይጠናቀቃሉ።

የወንጌል ንቅናቄ
የከፍታ ጣሪያ የቤተክርስቲያን ተከላ ፕሮጀክት ንቅናቄ የሚሆነው ስነምህዳሩ የሚጠይቃቸው ግብዓቶች እና ቅድመ ሁኔታዎች ሲሟሉ እና ቤተክርስቲያኖች ከዜሮ ተነስተው በቀጣይ አመታት ቤተክርስቲያን ለመትከል ቁርጠኝነት፣ ብቁ መሪዎች እና አመለካከት ሲኖራቸው ነው። ወደዚህ የከፍታ ጣሪያ ላይ ሲደርሱ እራሱን ችሎ የሚንቀሳቀስ አቅም እና ጉልበት የፈጠረ ንቅናቄ ይጀመራል ማለት ነው። ያለ ማንም ማዕከላዊ ትዕዛዝ ሰጪነት እና አሳዳዚነት አዲስ ባመኑ አማኞቸች እና መሪዎች ይህ ንቅናቄ ይቀጥላል ማለት ነው። በከተማ ያለች ቤተክርስቲያን እራሷን የምታቋቁም ናት መሪዎችን ማብቃት በቂ የሆኑ ስልጠናዎችን የማዘጋጀት አቅም አላት። ጥቂት የማይባሉ ቁጥር ያላቸው መሪዎች በየግዜው እየተነሱ ነው። በየሰባት ወይም አስር ዓመቱ የአማኞች እና የቤተክርስቲያን ቁጥር በሁለት እጥፍ ይጨምራል።

የከተማ የከፍታ ጣሪያ

የወንጌል እንቅስቃሴ የከፍታ ጣሪያ እጅግ አስፈላጊ ግብ ነው። ነገር ግን ሌላም የሚቀር ነገር አለ። የወንጌል እንቅስቃሴ ከፍተኛ ደረጃ ላይ ሲደርስ ስነምህዳሩ አድጎ በክርስቶስ ስጋ ( ቤተክርስቲያን) የ ሙሉ ከተማው የ ከፈታ ነጥብ ሊሆን ይችላል ። ይህ ወቅት በወንጌል እውነት ያደጉ እና በክርስቲያናዊ ስብእና የጎበቱ አማኞች ቁጥር የሚጨምርበት በማህበራዊ ህይወት ውስጥ የሚታወቅና የሚያስመሰግን ተጽዕኖ የሚመጣብ ነው። አንዳንድ የማረሚያ ቤት አገልግሎቶች ሪፖርት እንደሚያሳዩት ከአጠቃላይ እስረኛዎች አስር በመቶ የሚሆኑት ታራሚዎች ክርስቲኖች በሚሆኑበት ወቅት የማረሚያ ቤቱ የትብብር ባሕል ይቀየራል፤ በተመሳሳይ ሁናቴም የአዲስ ነዋሪዎች ቁጥር ብዛት ከአምስት እስከ ሃያ በመቶ መካከል ሲገኝ ምነም እንኳን በአከባቢው ባሕል ላይ የሚመሰረት ቢሆንም የሌላ እምነት ተከታይ የሆኑ ጉረቤቶቻቸውን መለወጥ ይችላሉ። እንደ ማሳያም በኒውዮርክ ከተማ ቁጥራቸው በጥቂቱ ከአምስት በመቶ እስከ አስራ አምስት በመቶ የሚሆኑ እና ንቁ ተሳትፎ ያላቸው የማሕበረሰብ ክፍሎች በከተማው የሕይወት ዘይቤ ላይ የጎላ ተጽዕኖ ይኖራቸዋል።

እንዴት ያለ መንገድን ብንከተል የከተማ አቀፍ የወንጌል እንቅስቃሴ በጥንካሬ ማሳደግና ‹‹ከተማን- የመቀየር ከፍታ ላይ በመድረስ በከተማው ባሕልና የኑሮ ዘይቤ ላይ የሚታይ ተጽዕኖን ሊፈጥር ይችላል። ይህ በእግዚአብሔር ጸጋ ድጋፍ መሆን እንደሚችል እናውቃለን። ለዚህም የታሪክ መጽሐፍት ምሳሌዎችን ይሰጡናል። ምንም እንኳን እንደ ጆን ዊስሊ ያሉ ጥቂት አገልጋዮች በእነሱ የተጀመረውን ስራ ለውጤታማነት ሲበቃ ማየት ታድለዋል። በከተማዎች ውስጥ የሚገኙ አብያተክርስቲያናት ይህንን ራዕያቸው ማድረግና በሙሉ አቅማቸውም መስራት ይኖርባቸዋል፤ ነገርግን በእነሱ የሕይወት ዘመን ለማየት መጠበቅ አይኖርባቸውም። ከተማችን በክርስቶስ ወንጌል ተደርሳ ማየት ከፈለግን ይህ በመጠበቅ እና በመረጋጋት መካከል ያለው ትክክለኛ ሚዛን ነው።

ምንጭ :- ሉዛን ሙቭመንት,2010
ትርጉም :- ምህረት በቀለ

# የወንጌል ስርጭት እና የአዲስ አበባ ከተማ ጉዳይ

«የአዲስ አበባ ከተማ ጉዳይ» ብዙ አይነት አንድምታዊ ፍቺዎች የሚሰጡት ጉዳይ ከሆነ ሰነባብቷል። ከከተማው ማንነት ፣ አመሰራረት ፣ ባለቤትነት እና የሕዝብ ስብጥር ጋር ተያይዞ የሚነሱ ጉዳዮች ከሃገሪቱ የዕለት ዜናዎች አመዛኙን ይሸፍናሉ። ይህ መልክዓ ምድራዊ እና ፖለቲካዊ ጉዳይ ውሎ አድሮ የቤተክርስቲያን እና በአዲስ አበበ የሚገኙ አማኞችም ጉዳይ መሆኑ አይቀሬ ነው።

ከመልክዓ ምድራዊ፣ የሕዝብ እና የባህል ስብጥር (ዴሞግራፊ) እና የፖለቲካ ጡዘቱን ተመልክተን ወደ ክርስትና ተልዕኮ ቀና ስንል ደግሞ አዲስ አበባ ለወንጌል ተልዕኮ በየጊዜው አዳዲስ ተግዳሮቶች እና ዕድሎችን እየፈጠረች ያለች ከተማ መሆኗን እናስተውላለን። በዚህ ፅሁፍ ከተሜነትን ፣ የወንጌል ተልዕኮን እና አሁን በአዲስ አበባ ከተማ የሚታዮ ጊዜያዊ እና ቋሚ ሁኔታዎችን እንዳስሳለን።

<u>ከተሜነት እና ክርስትና</u>

ከተሜነት (Urbanization) የከማነት መስፋፋትን የሚያመለክት ሀሳብ ሲሆን ከስልጣኔ ፣ ሃገራዊ እና አከባቢያዊ እድገት (በተለይ የኢኮኖሚ) ጋር የሚገናኝ ነው። ከተሜነት እንደሚባለው የአለም መደምደሚያ ነው። ሁሉም አከባቢ በጊዜ ሂደት ወደ ከተማነት እየተቀየረ እንደሚሄድ የማህበረሰብ አጠኚዎች ያመለክታሉ።

ግማሽ የአለማችን ህዝቦች የሚኖሩት በከተሞች ሲሆን ከእነዚህም መሃል የኢስያ ከተሞች (እንደ ቶኪዮ ፣ ጃካርታ ፣ ዴልሂ ፣ ሴዑል እና ማኒላ) በህዝብ ብዛት ይታወቃሉ። በተባበሩት መንግስታት ጥናታዊ ትንበያ መሰረት በእ.አ.አ በ2030 ከአለማችን ህዝቦች ወደ አምስት ቢልዮን የሚጠጉት በከተማ የሚኖሩ ይሆናል። ከእነዚህም መሃል አብዛኞቹ በአፍሪካ እና በኢስያ ከተሞች ይኖራሉ ተብሎ ይጠበቃል።
ከተሜነት ሊገፋ የማይችል ሃይል ሆኖ በፊት ያልተደፈሩ አካባቢዎችን ሳይቀር በቴክኖሎጂ እየቀየረ በንግድ ፣ በባህል እና በኑሮ እያስተሳሰረ ከአከባቢ አከባቢ እየተዛመተ ይገኛል። ለመሆኑ መፅሃፍ ቅዱስ ከተሜነትን እንዴት ያየዋል? ከተሜነትን በተመለከተ መፅሃፍ ቅዱስ የሚደግፈውም የሚኮንነው ጉዳይ ሆኖ በግልፅ ባናነብም የከተሞችን አመሰራረት ግን መፅሃፍ ቅዱስ በአብዛኛው ቦታ ያስቀምጣል። በተለይ በኦሪት የከተሞች አመሰራረት የአባቶች (Patriarchal cities) የሚባለው እንደሆነ እናነባለን። አብዛኞቹ የመካከለኛው ምስራቅ ከተሞች የተመሰረቱት በአባወራዎች ሰፋሪነት እንደሆነ እና የአከባቢውም ስም በአባወራዎቹ ወይንም አባወራዎቹ ባወጡት ስያሜ እንደሚጠራ እናነባለን።
ከዚህ በተረፈ የሰዎች የአሰፋፈር ስልትም ሁለት አይነት መልክ ሲኖረው አንደኛው ከአከባቢያዊ ምቹነት ጋር የተቆራኘ ሲሆን ሌላኛው ደግሞ ከአምላካዊ ምሪት ጋር ነው። አብዛኞቹ የጥንት ከተሞች ከአከባቢያዊ ምቹነት ጋር በተቆራኘ መልኩ የተመሰረቱ ነበሩ። ለዚህም የሎጥን ከአብርሃም ተለይቶ ሲሄድ የመረጠውን ምርጫ እንደምሳሌ ማንሳት ይቻላል (ዘፍ 13:5-13) ሎጥ የለመለመውን ነበር የመረጠው። ሁለተኛው አመሰራረት ደግሞ አባቶች በአምላክ ምሪት ተመርተው የጀመሯቸው ከተሞች ናቸው። ለምሳሌ ያህዌ በሙሴ በኩል «ማር ወደ ምታፈሰዋ ምድር» ሲወስዳቸው የእስራኤል አሰፋፈር ከxከባቢያዊ ምቹነት ጋር ብቻ ሳይሆን ከያህዌ ምሪት ጋር እንደሚገናኝ እንመለከታለን።
ስለዚህም በአጠቃላይ ታሪካዊ የመጽሐፍ ቅዱስ ከተሞች አመሰራረት የአባቶች ሞዴል ሲሆን ከዚያ ባለፈ ደግሞ የከባቢ አየር ምቹነትን እና የአምላክን ምሪት የተከተለ እንደነበር መመልከት ይቻላል። ወደ አዲስ ኪዳን ስንመጣ የከተሞች አመሰራረትን ባናገኝም የከተሜነት መስፋፋትንና ማደግን ግን እንመለከታለን። በአዲስ ኪዳን መጻህፍት ሰፍረው የምናገኛቸው ከተሞች በብሉይ ከነበሩት በስነ ህንፃ፣ በአስተዳደር እና በኢኮኖሚ ልቀው የሚገኙ ናቸው። ለዚህም ኢየሩሳሌምን ራሱ እንደምሳሌ ማንሳት እንችላለን። ኢየሩሳሌም ከብዙ መፈራረስ በኋላ በድጋሜ በመገንባት ከታሪካዊ በቅጥር የታጠረ ስፈራዋ የሰፋችበት ሁኔታ ተፈጥሯል።

ሌላው በአዲስ ኪዳን የምናገኘው የከተማን እና የክርስትና አሰፋፍ ግኙኙነትን ነው። ይህም ከክርስቶስ ተልዕኮ አንስቶ (ክርስቶስ የገጠር ከተሞች ላይ አተኩሮ መልዕክቱን ያደርስ ነበር) እስከ ሐዋርያዊ ተልዕኮዎች ድረስ ከተሞች የወንጌል ተልዕኮ ማዕከል እንደነበሩ ነው። ሐዋርያው ጳውሎስ ወንጌልን በከተማ የማድረስ ሞዴል የሚጠቀም ሰው እንደነበር ከተልዕኮዎቹ ማየት እንችላለን። በተለምዶ የሐዋርያው ጳውሎስ ሶስት የሚስዮን ጉዞዎች የምንላቸው አብዛኞቹ የተደረጉት በከተሞች ነበር። እንደ ኤፌሶን ፣ ተሰሎንቄ ፣ ቆሮንቶስ ፣ ፊልጲስዮስ ባሉ ትልልቅ ከተሞች በመስበክ ሐዋርያው በከተሞች ያለውን የወንጌል አስፈላጊነት አሳይቷል።
የኤፌሶን ተሞክሮው እንደሚያሳየው ደግሞ ዋና ከተሞች ለሌሎች ተቀራራቢ የገጠር ከተሞች በወንጌል መደረስ ያላቸውን ትልቅ ሚና እናያለን። ጳውሎስ በኤፌሶን ለሁለት አመት ተኩል ሲገለግል መላው ትንሹ ኢስያ ወንጌል እንደሰማ እናያለን (ሐዋ 19:)። ይህም በጊዜው ወደ 15 ሚልዮን ህዝብ ይገመታል። ይህ ህዝብ ይህንን መልዕክት እንዴት ሰማ ብንል በኤፌሶን በጢራኖስ አዳራሽ ይደረግ የነበረው የሐዋርያው አገልግሎት መልዕክቱ በሰዎች አማካይነት ከዚያ በመስፋፋቱ ሌሎች የገጠር ከተሞችን እና አካባቢዎችን በመድረሱ ነበር።

የቀጠለ....

# የወንጌል ስርጭት እና የአዲስ አበባ ከተማ ጉዳይ

በተለይ የሐዋርያው ጳውሎስ አገልግሎት ስለከተሞች የአዲስ ኪዳን ሚና ብዙ የሚነግረን ነገር አለ። ሐዋርያው ጳውሎስ በዘመኑ የተከላቸው አብያተክርስቲያናተ ቢበዛ ከ 14 እንደማይበልጡ ይነገራል። ከእነዚህ መካከል ሁሉም ማለት ይቻላል በጊዜው የተተከሉት በከተሞች ነበር። ነገር ግን የሐዋርያው የአገልግሎት ተፅዕኖ መላው አውሮጳን እና ኢስያን ያጥለቀለቀ እንዲሁም ዛሬም ድረስ የሚነገትለት ሆኗል። ይህ የሆነው ግን በመልዕክቱ ይዘት ብቻ ሳይሆን ሐዋርያው የተጠቀመው ከተሞችን የመድረስ ሞዴል ያመጣው ውጤት ነው።

ሐዋርያወ ጳውሎስ ከተሞችን በወንጌል በመድረስ ሶስት አይነት ስኬቶችን አስመዝግቧል። የመጀመርያው የሰለጠነውን (የተማረውን) ማህበረሰብ መድረስ ነው። ይህን ከአቴና ፣ ቤርያ እና ኤፌሶን ማየት ይቻላል። የሚመራመሩ፣ የሚፈላሰፉ እና የሚጠይቁ ሰዎችን እንዲያገኝ ረድቶታል። ሁለተኛው አይሁድንም አህዛብ የተባሉትንም (Multiethnic) እንዲያገኝ ረድቶታል። ይህን በተለይ በገላትያ ከተሞች ሚስዮን ማየት ይቻላል። ኋላ ህግ አጥባቂ የአይሁድ መምህራን መጥተው ያወኳቸው ቢሆንም ሐዋርያው አይሁድንም አህዛብንም ለመድረስ አስችሎታል ይህም የሐዋርያውን አገልገሎት ብሔርብሔረሰባዊ አደርጎታል። ሶስተኛው ደግሞ በኢኮኖሚ ሻል ያለውን ማህበረሰብ እንዲደርስ አስችሎታል። ይህም ለቀጣይ አገልግሎቱ ስኬት ርዳታን በማግኘት (ምሳሌ ፊልጲስዮስ ፤ ፊል 4:) እንዲሁም በረሃብ ለተጎዱት ገንዘብን በመሰብሰብ ረድቶታል (ምሳሌ መቄዶንያ: 2ኛ ቆሮ 7:)። ከዚህም ባለፈ ነጋዴዎችን ማገልገል ለወንጌሉ ወደ ሌሎች የገጠር ከተሞች መስፋፋት ትልቅ ሚናን ተጫውቷል።
ለማጠቃለል ከተማ ፣ ከተሜነት እና ክርስቲያናዊ ተልዕኮ በብሉይም ይሁን ሃዲስ ኪዳን እጅግ ቁርኝት ያላቸው ጉዳዮች ናቸው። በብሉይ የእምነት አባቶች ከተሞችን በያህዌ ምሪት መሰረቱ ፤ በሃዲስ ሐዋርያዊ አባቶች በመንፈስቅዱስ ምሪት ከተሞችን በወንጌል ደረሱ። ከዚህ እውነታ በመነሳት የአዲስ አበባን ጉዳይ ከክርስቲያናዊ ተልዕኮ (በተለይ የሐዋርያው ጳውሎስ ሞዴል) አንፃር በአጭሩ ለመቃኘት እንሞክር።

<u>አዲስ አበባ እና የወንጌላውያን ክርስትና</u>
አዲስ አበባ የተጣራ መረጃ አሁን ላይ በይኖርም በግምት ከ 5-6 ሚልዮን የሚጠጋ ህዝብ የሚኖርባት የራሷ አስተዳደር ያላት፣ የፈፀደራል መንግስቱ መቀመጫ እንዲሁም የኢትዮጵያ ዋና ከተማ ፣ የአፍሪካ ህብረት መቀመጫ እንዲሁም የኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስተረ ዋና መቀመጫ ነች። የእነዚህ ሁሉ መቀመጫ መሆኗ ታዲያ የከተማይቱን ውቅር እና የነዋሪዎቹን አሰፋፈር ፣ አቀማመጥ ፣ ባህላዊ ስብጥር እና ፖለቲካዊ አመለካከት ላይ ተፅዕኖ የሚያሳድር ጉዳይ ነው። ስለዚህም ስለ አዲስ አበባ ስናወራ እነዚህን እውነታዎች ከግምት በማስገባት መጀመር አለብን።

አዲስ አበባ ለኢትዮጵያ የወንጌል መነሻ ባትሆንም ከመጀመርያዎቹ መካከል ነበረች። በ19ኛው ክፍለ ዘመን የወንጌላውያን ክርስትና ወደ አቢሲኒያ/ኢትዮጵያ የገባው በብዙ መንገዶች ሲሆን አዲስ አበባ የወንጌል ማዕከል የሆነችው ከ 1920 በኋላ ማለትም ከአፄ ሃይለስላሴ ወደ ስልጣን መምጣት በኋላ ነበር። በጊዜ በሸዋ ክፍለ ሃገር የነበረችው አዲስ አበባ ብዙ ሚስዮናውያን ገጠር ከፍተዋቸው የነበሩ የሚስዮን ጣቢያዎቻቸውን ወደ ከተማ እንዲያመጡ እና ከመሃል ህዝብ ጋር እንዲተዋወቁ ከተማይቱ እድል ፈጥራለች። ያም ሆኖ አዲስ አበባ ለወንጌላውያን ክርስትና ክፍት ነበረች ብሎ መናገር እጅግ ይከብዳል። በአፄውም ዘመን ይሁን በደርግ ዘመን በወንጌላውያን አማኞች ላይ በከተማይቱ ስደት እና መዘጋት እስከ መደብደብ እና ሞት ድረስ ደርሷል። አብዛኛው ስደትም ከኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ እና ከደርግ ባለስልጣኖች በተለያየ ጊዜያት የመጣ ነበር።
እ.አ.አ በ2007 የህዝብ እና የቤቶች ቆጠራ መሰረት ከከተማው ህዝብ 7% ብቻ ነው የወንጌላውያን እምነትን የሚከተለው። ከ80 ዓመታት በላይ የዘለቀው የወንጌላውያን ክርስትና ብዙ ውጤት ማሳየት ያልቻለበት ዋና ምክንያት በወንጌላውያን ላይ ይደርስ የነበረው ስደት እንደነበር ሊዘነጋ አይገባውም።
ከዚህ ባለፈ ግን ሌላኛው ትልቁ ችግር የወንጌላውያን ሚስዮናውያን ገጠር ላይ ብቻ ትኩረት ተደርጎ የተሰራው የወንጌል ስራ ነው። በ1935 አፄ ሃይለስላሴ ከእንግሊዝ እንደተመለሱ ለውጭ ሚስዮናውያን የኦርቶዶክስ ቤ/ክ በሌለችበት (ደቡብ ፣ ምዕራብ እና ምስራቅ ኢትዮጵያ) ቦታ እንዲሰሩ ፈቃድ ሰጥተው አዲስ አበባ ላይ ግን ሁሉም በነፃነት እንዲንቀሳቀሱ ፈቅደው ነበር። ሆኖም የሚስዮናውያኑ ትኩረት እንዲሁም አልፎ አልፎ ከንጉሱ ከራሳቸው በሚመጣ ጫና ወደ ገጠር ላይ እንዲሰማሩ ሆኗል። ይህ የገጠር አገልግሎት እጅግ ውጤታማ የነበረ ቢሆንም ወንጌላውያን ክርስቲያኖች ከተማ ላይ ተፅዕኖ ፈጣሪነታቸው ሳይጎላ በመቅረቱ ጫና ውስጥ እንዲወድቁም አደርጓቸዋል።

ከ1983 ወዲህ አዲስ አበባ ላይ የተለያዩ የወንጌላውያን አብያተ ክርስቲያናት ተከፍተው እንቅስቃሴዎች ተደርገዋል። ምንም እንኳ የኦሮቶደክስ ጫና ባይቀንስም ወንጌላውያን ክርስቲያኖች በሚታይ እና ተጨባጭ በሆነ መልኩ እድገት እያሳዩ እንደሆነ አይካድም። ነገር ግን ዛሬም ቢሆን አዲስ አበባነ በወንጌል ከመድረስ አንፃር ብዙ ተግዳሮቶች አሉ። እነዚህን ተግዳሮቶች እና ሐዋርያዊ ምላሾችን በአጭሩ ልዳስ እና ፅሁፌን ፅቋጭ።

ወደ ገጽ 11 ዞሯል...

# ከተሞችና መልካም አጋጣሚዎቻቸው

## የማዕድኑ ክምችት መሿለኪያ መንገድ

ከተማን ሳስብ “ከተመ፣ ሰነበተ፣ ዋለ፣ አደረ” የሚሉ ቃላቶች ይታወሱኛል። ሰዎች ከቀዬያቸው በተለያየ አጋጣሚ በመራቅ ለኑሮ ምቹ በሆነ ስፍራ ላይ ይከትማሉ። በዚያም የከተሙ ከተሜዎች ከተማን ይሰራሉ።

እኔ ተወልጄ ያደኩት ከአዳማ 7 ኪ.ሜ ርቀት ላይ የምትገኝ ወንጂ በምትባል አንስተኛ ከተማ ውስጥ ነው። ወንጂ የምትታወቀው በምርቷ ስኳር እና ደስታ ከረሜላ ነው። ወንጂን እንድወድ ካደረጉኝ ምክንያቶች መካከል ዋነኛ ለስራ ከተለያየ የኢትዮጲያ ክፍል የመጡ ሰዎች መገኛ በመሆኗ ጭምርም ነው። እያንዳንዱ ሰው የመጣበትን አካባቢ ይወክላል። ትንሿ ኢትዮጲያ የሚል መጠሪያም አላት።

እነዚህ የከተሙትን ሰዎች በወንጌል ለመድረስ በወንጂ ብዙ መልካም አጋጣሚዎች አሉ። በመንፈሳዊ እንቅስቃሴም በኩል ከተለያዩ ስፍራ ለስራ የመጡ አብዛኛዎቹ በከርስቶስ ኢየሱስ የማመን እድላቸው የሰፋ ነው። በክርስቶስ ያመኑት ሰዎች ወደ መጡበት ቀዬአቸው ሲመለሱ የተቀበሉትን ወንጌልም ጭምር ይዘው ይመለሳሉ። እነዚህ ሰዎች የወርቁ ማዕድን በብዛት ወደ ተከማቸበት ስፍራ የሚመሩን ናቸው።

ከወንጂ በተሻለ የዚህ የማዕድኑ መሿለኪያ መንገድ ሰፊ እድል አዳማ{ናዝሬት} አላት፤ ከአዳማ ደግሞ አዲስ አበባ የሰፋ መልካም አጋጣሚዎች አሏት። የሰሜን፣ የምስራቅ፣ የደቡብና የምዕራብ የኢትዮጲያ ክፍል ሕዝቦች በአዲስ አበባ ውሰጥ በስፋት ይገኛሉ። በአንዳንድ የአዲስ አበባ ክፍለ ከተማ ሰፋሪዎቹ በብዛት በመገኘታቸው ስፍራው በስማቸው እስከ መጠራት ይደርሳል። የትኛው የሕዝብ ክፍል በየትኛው የአዲስ አበባ ቦታ እንደሚገኝ ይታወቃል። ለምሳሌ ቦሌ ሚካኤል አካባቢ በብዛት የሶማሊ ክልል ተወላጆች ይገኛሉ። እዚህ ስፍራ ላይ የሚገኙ የሶማሊ ተወላጆች ወደ ሰፊው የሕዝባቸው ክፍል ለመድረስ መንገዶች ናቸው።

ወደ ከተሞች የሚደረገው የሕዝብ ፍልሰት የራሱ የሆነ አሉታዊ ተፅዕኖ ቢኖረውም ከተልዕኮ አኳያ ስንመለከተው የሰፋ መልካም አጋጣሚ ነው። እኔ ባደኩበት አካባቢ ካለው የሕዝብ ፍልሰት ይልቅ ወደ ሰፋፊ ከተሞች የሚደረገው ፍልሰት እጅግ ብዙ በመሆኑ የእያንዳንዱን የሕዝብ ክፍል የማግኘት አጋጣሚው በቀላሉ ነው።

በከተሞች ውስጥ የምትገኘው ቤተክርስቲያን የክርስቶስ ሕዝቦችን ሁሉ የማዳኑን ወንጌል ለማደረስ ይሄ አይነት አጋጣሚ በደጇ እያንኳኳ ነው።

ሶማሊ ክልል ሄዶ በዛ ለሚገኙ የኢሳ ጎሳዎች ወንጌልን ለመናገር ከባድ ሁኔታ አለ። ነገር ግን ከዛ ጎሳ በስራም ይሁን በተለያየ ሁኔት ወደ ከተሞች የሚመጡ ሰዎች በከተማቾን ውስጥ ይኖራሉ። አንዳንዱ የስራ ባልደረባችን፣ ሌላኛው የቤታችን ተከራይ፣ ሌሎኞቹ ደግሞ የሱቅ ደንበኞቻችን ይሆናሉ።

አሁን ባሉበት ሁኔታ ለእነርሱ የወንጌልን እውነት ለማስረዳት የተመቻቸ አጋጣሚ አለ። እነዚህ ሰዎች ወንጌልን ከተቀበሉ በዋላ ወደ ሕዝባቸው ተመላሽ ሚስዮናዊ ናቸው።

ወደ ዋና የማዕድን ስፍራ የሚወስደውን መንገድ ማግኘት ብዙ አላስፈልጊ ልፋቶችን ከመቀንስ ባለፈ ሀብትና ጊዜይቸንን ይቆጥብልናል። ደግሞም እጅግ ውጤታማ ስልትም ነው። ኢየሱስ ከሰማሪያዊቷ ሴት ጋር በነበረው ቆይታ የተጠቀመው ይህን አይነት ስልት ነው። የሰማሪያ ከተማን ሰዎች በሴቲቱ በኩል አግኝቶአቸዋል።

ማዕድኑን ሙሉ በሙሉ ለማውጣት የምንሄድበት መንገድ በጥንቃቄ ሊሆን ይገባል። አጠገባችን ያለውን ሰው ባህል በሚገባ ማወቅና ወንጌልን ብቻ ማስተላለፋችንን እርግጠኞች መሆን አለብን። ምክንያቱም ከከተማ ወደ ሕዝባቸው በሚመለሱበት ጊዜ ከወንጌል ጋር የኛን ባህል ቀይጠን ከሰጠናቸው ማዕድኑን በሙሉ ልናግኝ አንችልም። ስለዚህ አጠግባችን ያለው ሰው ባህሉን ሳይለቅ እንዴት ወንጌልን ልናደርሰው እንደምንችል ሆን ብልን ማሰብ አለብን። ይህን ስልት ኢየሱስ ከሰማሪታዊቷ ሴት ጋር ያደረገውን ቆይታ እንመልከት። {ዮሐ 4}

- ሆን ብሎ በሰማሪያ አለፈ።
- ሆን ብሎ በምንጩ አጠግብ ተቀመጠ።
- ሆን ብሎ ንግግር ጀመረ።

ኢየሱስ ምስክርነቱ ያነጣጠረው ሴቲቱ ላይ ነበር። ከጥቂት ምልልስ በዋላ ሴቲቱ በእርሱ አመነች። ወደ ከተማም ገብታ ያመነችውን ብቻ መሰከረች። በሴትየዋ ላይ ምንም አይነት የባህልና የውጫዊ ስርአት ለውጥ ሳይኖር በሕዝቧ ውስጥ ገብታ የተለወጠውን ሕይወቷን ስትመሰክር ሰው ሁሉ ተከተላት። ኢየሱስ ወደ ዋናው የወርቅ ማዕድን ክምቸት ወዳለበት ስፍራ በዚህች ሴት አማካኝነት ደረሰ።

የቀጠለ....

የሶማሊ፣ የአፋር፣ የጉጂ፣ የቦረና፣ የራያ፣ የወሎ፣ የቦዲ፣ የጉምዝ እና ከሌሎችም ሕዝቦች የመጡ ጓደኞቻችን ይኖራሉ። እነዚህን ስናስብ ከነርሱ ጀርባ ብዙ ማዕድን እንዳለ ልናስብ ይግባናል። ሙሉ ማዕድኑን ለማውጣት ከፈለግን አጠገባችን ያለውን ወርቅ "አገኘውት" ብሎ አደባባይ ከማውጣት የወርቁ ክምችት ያለበት ስፍራ እስክንደርስ ድረስ በሚስጢር ይዞ መጓዙ ወጤታማ ስልት ነው።
ሀሳቤን ሳጠቃልል ከተሞችን በተልዕኮ መነፅር ከተመለከትናቸው ደጃፋቻን ላይ የተዘረገፉ እጅግ ብዙ ጥቅል ሀብቶች የያዙ ናቸው። የከተማ ቤተክርስቲያን እና አማኞች ይህን የማዕድኑን ክምችት ስፍራ ለማግኘት በደጅችን ያለውን መልካም አጋጣሚ እንጠቀም። ተባረኩ!

አቤኔዘር ጌታቸው
የተልዕኮ አስተማባሪ

ከገጽ 8 የቀጠለ....

# የወንጌል ስርጭት እና የአዲስ አበባ ከተማ ጉዳይ

## አዲስ አበባ እና የወንጌል ተልዕኮ ተግዳሮቶች

ወንጌሉን ለአዲስ አበባ ህዝብ ማድረስን ስናስብ ከሚመጡ ወሳኝ ጉዳዮች (variables) ጥቂቶቹን ማስታዋስ ያስፈልጋል። ሶስት መሰረታዊ እና ጊዜያዊ ወሳኝ ጉዳዮች ከአዲስ አበባ ጋር ተያይዘው መነሳታቸው አይቀርም። 1) የህዝብ ቁጥር እድገት 2) የህዝብ ስብጥር ልዩነት 3) የ(ድህረ) ዘመናዊነት ዕድገት ናቸው።

**1) የህዝብ ቁጥር ዕድገት**

በዚህ ጊዜ እንደ መንግስትም እንደ ህዝብም ሰፊ ትኩረት ያልተሰጠው ጉዳይ ቢኖር የህዝብ ቁጥር ዕድገት ነው። ኢትዮጵያ በዓመት 2ሚልዮን ህዝብ እየጨመረች ያለች በዓለም ላይ በፍጥነት እየጨመሩ ካሉ የህዝብ ቁጥሮች መካከል ከመጀመሪያዎቹ የምትመደብ ሃገር ሆናለች።

የዚህ ተፅዕኖ በከተማይቱ ላይ በሰፊው ይንፀባረቃል። አሁን ላይ አዲስ አበባ እጅግ በጣም ብዙ ህዝብ መኖርያ ሆናለች። በግምት ከላይ ከተቀመጠው 5–6 ሚልዮን በተለያ እስከ 9 ሚልዮን የሚስስቀምጡ ሰዎች አሉ።

ለዚህ የከተማው የህዝብ ብዛት መጨመር ምክንያቶቹ ሶስት ናቸው። አንደኛው ከላይ እንደተጠቀሰው ሃገራዊ የሆነው የህዝብ ብዛት መጨመር ሲሆን ይህም ከመዋለድ ጋር ይያያዛል (Biological growth) ። ሁለተኛው ደግሞ የሀገር ውስጥ ፍልሰት (local/national migration) ነው። ከገጠር ኢትዮጵያ ወደ አዲስ አበባ ብዙ ሰዎች እየፈለሱ ነው። አብኞቹ ለስራ የሚፈልሱ ሲሆኑ ከቀያቸው በመፈናቀላቸው ምክንያት የሚፈልሱም አሉ። ሶስተኛው ደግሞ አለምዓቀፍ ይዘት ያለው ፍልሰት ነው (International migration) ። ይህ በተለያ ከቅርብ ዓመታት ወዲህ እጅግ እየጨመረ ያለ ጉዳይ ነው። አሁን ላይ ኤርትራውያን ፣ ሶማሌያውያን ፣ ሶርያውያን ፣ ደቡብ ሱዳናውያን ከሃገራቸው ወደ ኢትዮጵያ በተለይም ወደ አዲስ አበባ በብዛት እየፈለሱ ይገኛሉ። አብዛኞቹ በሰላም ዕጦት፣ በችግር ምክንያት የሚፈልሱ ናቸው።

የአዲስ አበባ ህዝብ ቁጥር መጨመር የቤቶች እና የአኗኗር ሁኔታ ሁኔታ ላይ ተፅዕኗ አሳድሯል። አብዛኛው ህዝብ ወደ ኮንደሚንየም ኑሮ እየተቀላቀለ ይገኛል። ይህ ደግሞ ኗሪውን ከመድረስ አንፃር ራሱን የቻለ ትልቅ ተግዳሮትን ትዞ መጥቷል።

አብዛኞቹ ኮንደሚንየሞች በአዲስ አበባ ጫፍ ላይ እንደመገኘታቸው በነዚህ አከባቢዎች የአዳዲስ አብያተክርስቲያናትን አስፈላጊነት ጨምሮታል።

**ሐዋርያዊ ምላሽ:–** የአዲስ አበባን ህዝብ ቁጥር መጨመር በተመለከተ ሐዋርያዊ ምላሽ የአብያተ ክርስቲያናት ቁጥርን መጨመር ሊሆን እንደሚችል ጥርጥር አይኖርም። ነገር ግን የአብያተ ክርስቲያናቱ ቁጥርን በመጨመር እና አዳዲስ አብያተክርስቲያናትን መተከል የማይደግፉ «ቤተ ክርስቲያንን ሱቅ አደረጋችኋት» የሚሉ አይጠፉም። ሆኖም ግን ታዋቂው የሚስዮን አጥኚ C. Peter Wagner ለመጠቀስ «ቤተ ክርስቲያን ተከላ ከሰማይ በታች ውጤታማ የወንጌል ማዳረሻ ዘዴ ነው» የሚለውን ሃሳብ በፍፁም ፅበፀ ደግፈዋለሁ። ዛሬም እየጨመረ ላለው ህዝብ ቁጥር በወንጌል መደረስ መፍትሄው አብያተክርስቲያናትን በተጠና ሁኔታ መትከል ነው።

የአብያተክርስቲያናቱ አተካከል በጥናት ፣ አውዱን በጠበቀ እና በመለኮት ምሪት ከሆነ ብዙዎችን መድረስ ይቻላል ብዬ አምናለሁ።

**2) የህዝብ ስብጥር ልዮነት**

የአዲስ አበባ ህዝብ ስብጥር የዛሬ 50 ዓመት ከነበረው ዛሬ ላይ ይለያል። ይህም ከላይ በጠቀስኳቸው ፍልሰቶች ምክንያት ነው። ከገጠር እንዲሁም ከሌሎች ሃገራት ወደ ከተማይቱ ሰው እጅጉን ስለሚፈልስ የከተማይቱን የባህል (የህዝብ አይነት ፣ የቋንቋ ወዘተ) ይዘት በየጊዜው ይቀያይረዋል።

አሁን ላይ በአዲስ አበባ አማርኛ ፣ ትግርኛ እና አፋን ኦሮሞ በስፋት ይነገራሉ። ጉራጊኛ እና ሶማልኛም እንዲሁ። በተለይ ትግርኛ እና ሶማልኛ ቋንቋዎች በስፋት መነገር ከኤርትራውያን እና ሶማልያውያን ፍልሰት ጋር በቀጥታ ይገናኛል። አፋን ኦሮሞም በላፉት ጥቂት አመታት በተለይ ከፖለቲካ ሁኔታው ጋር ተያይዞ በከተማዩቱ የተናጋሪዎቹ ቁጥር ጨምሯል። ይህ ለክርስቲያናዊ ተልዕኮ ሌላኛው የተረኩረት አቅጣጫ ነው።

**ሐዋርያዊ ምላሽ:–** በአዲስ አበባ እያየለ ለመጣው የሕዝብ ስብጥር ልዮነት ሐዋርያዊ ምላሽ የሚሆነው የአብያተክርስቲያናት አተካከልንና ሁኔታን አውዳዊ ማድረግ ነው። ይህ በተለይ ቋንቋን ይመለከታል። በአዲስ አበባ በተለያየ ቋንቋ መደበኛ ፕሮግራም የሚያደርጉ፣ የሚስያስተምሩ እና ደቀ መዝሙር የሚያደርጉ አብያተክርስቲያናት ያስፈልጋሉ።

ጎፋ መብራት ሃይል ፣ ጀሞ ፣ ሲ ኤም ሲ ወዘተ አከባበዊዎች ላይ የትግርኛ ተናጋሪዎች በብዛት ስላሉ በትግርኛ ቋንቋ የሚያገለግሉ አብያተክርስቲያናት መተከል አለባቸው። በአዲስ አበባ ጥግ ላይ አብዛኘው የአፋን ኦሮሞ ተናጋሪ ስለሆነ በተመሰሳይ በኦሮምኛ ቋንቋ የሚያገለግሉ አብያተክርስቲያናት ያስፈልጋሉ። በቦሌሚካኤል ፣ ሳሪስ አዲስ ሰፈር ደግሞ ሶማልኛ ተናጋሪዎች ስላሉ አውዱን እና የሶማሌዎችን ባህል በጠበቀ መልኩ ሶማልኛ ፕሮግራሞች ቢጀመሩ መልካም ነው። ይህ ለአዳዲስ አብያተክርስቲያንት ብቻ ሰይሆን አሁን ላይ ያሉትም ይህንን ቢተገብሩ እመክራለሁ።

በከተሞች የህዝብ ስብጥር መለዋወጥ የ21ኛው ክፍለ ዘመን ባህሪ ነው። አሜሪካ እና ያደጉት ሃገራት ፍልሰትን ለማስቀረት በፖለቲካው መድረክ ብዙ ይከራከራሉ። እኛም ሃገር ደርሶ ወደዚህ መመጣቱ አይቀሬ ይመስላል። ሆኖም ግን እግዚብሔር ያመጣልን ዕድል መሆኑንም መረዳት ትልቅ ነገር ነው በዬ አምናለሁ።

ለምሳሌ ያክል ከሶማሌ ክልል የተፈናቀሉ የሃረርጌ ኦሮሞዎች ዛሬ በአዲስ አበባ እና ዙርያው ሰፍረዋል። ጉዳዮ ምንመ አይነት ፖለቲካዊ አንድምታ ይኑረው እንደ ተልዕኮ ሰዎች ስናስበው ግን እነዚህን ህዝቦች ለመድረስ እጅግ ጥሩ አጋጣሚ ተፈጥሮልናል። ዛሬ ላይ ሚስዮናዊ ወደ ሃርጌ መላክ ላይጠበቅብን ይችላል እኛው አጠገብ እግዚአብሔር አምጥቷቸዋልና። ለሌሎች ህዝቦችም እንዲሁ።

የቀጠለ....

## የወንጌል ስርጭት እና የአዲስ አበባ ከተማ ጉዳይ

3) የ (ድህረ) ዘመናዊነት ዕድገት

ሶስተኛው እና የመጨረሻው የአዲስ አበባን ጉዳይ ስናነሳ የማንተወው ጉዳይ ቢኖር በአዲስ አበባ እየታየ ያለው የኑሮ እና የአስተሳሰብ ዕድገትን ነው። ይህ በቀጥታ ከምዕራባውያኑ ዕድገት ጋር ይያያዛል።
አዲስ አበባ የአፍሪካም መዲና እንደመሆኗ አለም አቀፋዊ ኩነቶች እና አመለካከቶች የሚንፀባረቁባት ከተማም ነች። ስለዚህም የምዕራባውያንን ባህል ያለ ብዙም ተግዳሮት ትቀበላለች። ዛሬ ስለ ፋሽን ፣ ውበት ፣ ጤና አጠባበቅ ወዘተ አዲስ አበባ የምዕራባውያኑን አካሄድ ከእነሱ ባልተናነሰ መልኩ ይዛበታለች። የተላያዩ የፍልስፍና አመለካከቶችም የከተማይቱ ወጣቶች ዘንድ ዘልቀው ገብተዋል። አዲስ አበባ መዘመኗ ባይከፋም መዘመንን ሳታጣጥም አልፋ ድህረ ዘመናዊነት ላይ መድረሷ ሌላ ትልቅ ተግዳሮት ይዞ እንደመጣ ማየት ይቻላል። የዮኒቨርሲቲዎች መብዛት እና የኢንተርኔት መረሽ ግንኙነት ለዚህ ትልቅ ሚና አላቸው።

ሐዋርያዊ ምላሽ፡– እያደገ የመጣውን ድህረ ዘመናዊነት አሽንፎ የአዲስ አበባን ህዝብ በወንጌል ለመድረስ ሐዋርያዊ ተልዕኳችን ለዚህ አላማ የተካነ (equipped) መሆን አለበት። የተማሩ ሚስዮናውየን እና የቤተክርስቲያን ተካዮች ከተማው ውስጥ ያስፈልጉናል። ነባርም ቢሆን አዳዲስ የሚተከሉ አብያተክርስቲያናት ይህን ከግምት ማስገባት አለበቸው። እዚህ ጋር በኒውዮርክ የሪዲምድ ፕረስፒቴርያን ቸርች መስራች የሆኑት ቲሞቲ. ኬለርን እንደምሳሌ በነሳ መልካም ነው። እርሳቸው በኒውዮርክር በ1980 ዎቹ ለመትከል ሲነሱ «አብደሃል እንዴ?» ተብለው ነበር። ምክንያቱም የኒውዮርክ ህዝብ ድህረዘመናዊ የተጠናወተው ለበፀተክርስቲየሰብ እጅ ያይሰጥ ነው ተብሎ ስለሚታሰብ ነበር። ሆኖም ግን የመጋቢ ቲሞቲ ኬለር የወንጌል አቀራረብ ለእንዲዘህ አይነት ማህበረሰብ የሚመች እና የሚመጥን ስለነበር ዛሬ ላይ ቤተክርስቲያናቸው ከ 5000 በላይ አባላት አሉት። እየሰለጠነ ላለው ማህበረሰብ ቀድመን መዘጋጀት እና መመገብ የሐዋርያዊ ተልዕኮው ስራ ሊሆን ይገባዋል።

መደምደሚያ

አዲስ አበባ ትልቅ ከተማ ነች። ብዙ ህዝብን ይዛለች። ብዙ አይነት ህዝብ ይኖርባታል። ወንጌል ለሁሉም ያስፈልጋል። ስለዚህም የሐዋርያውን ጳውሎስ የከተማ ወንጌልን የማድረስ ሞዴል በመጠቀም በከተሞች አብያተክርስቲያናትን በመትከል፣ በከተማው ውስጥ ለሚኖሩ ለተለያዩ ቋንቋ ተናጋሪዎች መልዕክታችንን እያደረስን እና ከስልጣኔ ጋር ተያይዘው የሚመጡ ተግዳሮቶችን በዕውቀት እየተጋፈጥን ወንጌሉን ለሁሉም ማድረስ እንችላለን። አዲስ አበባን ስንደርስ፣ ትግራይን በወንጌል መድረስ እንችላለን። አዲስ አበባን ስንደርስ ሃረርጌን እና ሶማሌን መድረስ እንችላለን። ከተማይቱን ማን መሰረታት ሳይሆን ማን በወንጌል ይድረሳት የሚለው ይበልጥ ሊያሳስበን ይገባል። ከተማይቱ ውስጥ ማን ይኖራል ከሚለው በላይ ለሚኖረው ህዝብ እንዴት ወንጌልን እናድርስለት? የሚለው ውስጣችንን ያነቃቃው።
አሜን!

ናኦል በፍቃዱ
(B.Th., MA in World Mission) የወንጌል ሰባኪ ፣ የመፀሐፍ ቅዱስ አስተማሪ

# የከተማን የደም ሥሮች መረዳት ለወንጌል ተልዕኮ

በምድር ላይ ያሉ ቁስ አካላት ሁሉ የአካሉ አቅም የምትፈትሽ አንድ ወሳኝ ቦታ ትኖራቸዋለች። ያቺ ቦታ ከተገኘች ቁስ አካሉን ማውደምም ማልማትም ቀላል ነው። ህንጻ ሊቅ ባልሆንም አንድ ህንጻ ሲገነባ የዚያ ህንጻ አውታሪ የሚሆኑ ከመሰረት አንስቶ እሰከ ህንጻው ጣሪያ ድረስ ከቀለም እና ብሎኬት መደርደር በፊት የህንጻ ቁመናው ( structure) ላይ ትኩረት ትሰጣለክ። ህንጻ የቀለሙ ውጤት አይደለም ፣ ገጽታውን የምንሸፍንበት ብሎኬትም እንደዛው ምክኒያቱም አንድ ግንባታ ያለነዚህ መልካ ባይኖረው እንጂ ቁመና ግን በርግጥ ይኖረዋል። ያለ መሰረት እና በየፍሎሩ የምናቆመው ኮለን ግን ህንጻ አለ ማለት አንችልም። ይህን ህንጻ ለማፍረስም ይሁን ለማደስ እነዚህ ሁለቱ የኛ ትልቁ ትኩረት፣ አቅም እና ብቃት የመፈስባቸው እና ትኩረታችንን የምንሰጣቸው ናቸው።

ከተሞችን እዴት በወንጌል እንድረስ የሚለው ጥያቄ የብዙ አገልጋዮች እና አማኞች ጥያቄ ነው። ከተማን በወንጌል ለመድረስ እስከ ዛሬ ባደረግናቸው ጉዞዎች የተጠቀምናቸው ስልቶች በቂ ካለመሆናቸውም ባሻገር ሌላ የተሸለ ስልት እንዳንፈልግም አድርገውናል። በዚህ ሒደት ለመና ችላ ያልናቸው ወይም አብዘትን ያልተጠቀምንባቸው መንገዶች በከተማ ውስጥ ያሉ የማህበረሰብ እና የህዝብ ክፍሎች ስብጥር መናሃሪያ የሆኑ ክፍሎችን ነው።

አንድን ከተማ ሲያልፍ ሃገርን የሚሞሉት ሰዎች ናቸው እነዚህ ሰዎች በህዝብ ክፍል ( ብሔር) እና በማህበረሰብ ክፍል ( የማህበረሰብ መሰባሰቢያ መንገዶች) ተሰባጥረው በከተማ ሲያልፍ በሃገር ደረጃ አብረው ለዘመናት ይኖራሉ። ለምሳሌ ያህል በኢትዮጵያ ያሉ አስሩን የክልል ዋና ከተማ ሆኑ ዘጠኙን ከተሞች ብንመለከት የክልሉ ብሔር በብዛት ከዚያም ሲያል ከተለያዩ የኢትዮጵያ ክፍሎች በስራ፣ ትምህርተ፣ ኑሮ እና በተለያዩ የህይወት አጋጣሚዎች ወደዛከተማ መጥተው ኑሮአቸውን የመሰረቱ ወንዶች እና ሴቶችን እናያልን በዚያ ከተማ አንድ ብዜር ብቻ አይኖርም ብዙ ብሔሮችን የሚወክሉ ብዙ ሰዎች ይኖራሉ። እነዚህ ሰዎች ደግሞ በሰራ፣ ትምህርት፣ ኑሮ እና የተለያዩ መልኮች በአንድም በሌላም ይገናኛሉ። ታዲያ ከተማ ደምስሮች የሚንለው ሰዎች የሚገናኙባቸውን እነዚህን ዘርፈ ብዙ መስኮች እና እድሎችን ነው።

የከተማን ደም ስሮች መረዳት ከተማን ብቻ ሳይሆን ያላተደረሱትን የህዝብ ክፍች በወንጌል ለመድረስ ቁልፍ ሚና ይጫወታሉ። ይህም ማለት በከተማ ውስጥ ለስራ የሚጣን የሶማሌ ተወለጅ በስራው ቦታ፣ በመኖሪያ ስፍራው እና በሌሎችም በማሀበረሰባዊ ግንኙነት መስኮች በወንጌል ልንደርሰው ትልቅ እድል ይሰጠና ስለሆነም አንድ ግለሰብ ብቻ ሳይሆን ስራው ጨርሶ ወደ መጣበት ፍራ ቢመለስ እንኳ ከእርሱ አልፋ ማህበረሰቡን ለመድረስ እድል ያለው ሰው ነው። ይህንን ምሳሌ በሰፊው በምናገኛቸው የትምህር ቤቶችና በኢትዮጵያውያን ዘንድ ቦታ የምንሰጠው የምህበረሰብ አብሮ ምኖር ባህል ለዚህ  ትልቅ መልካም አጋጣሚ የሚፈጥር ነው። ይህን ይበልጥ ለመረዳት ጢሞቲዎስ ሞንስማ የተጻፈ ማብራሪያን አስቀምጫለው ።

ብሔር ብሔረሰቦች

አንድ የከተማ ሚሲዮናዊ ማዕድን አውጪ ሊያገኛቸው የሚፈልጋቸው ሰዎች በብሔር ብሔረሰቦች ውስጥ የተካተቱ ናቸው። በከተሞች ውስጥ ከሚገኙ ብሔር ብሔረሰቦች ውስጥ የትኞቹ በወንጌል እንደተደረሱና የትኞቹ እንዳልተደረሱ ለይቶ ማወቅ በጣም ጠቃሚ ነው። በዛሬው ዘመን በብዙ ታላላቅ ከተሞች ውስጥ ብዙ አብያተ-ክርስቲያናት ያሉባቸው በሚመስሉትም እንኳን ከብሔር ማንነታቸው፣ ከቋንቋ ችግሮችና ከሌሎች ባህላዊ እንቅፋቶች የተነሳ ችላ የተባሉ ጥቂት ሕዝቦች ይኖራሉ።

በአንድ እስላሞች በሚበዙበት ሐገር ውስጥ አንድ ሚሊዮን ሰዎች የሚኖሩበት ከተማ ያለ ሲሆን በዚህ ከተማ ውስጥ 70 አብያተ-ክርስቲያናት አሉ። ላይ ላዩን ሲታይ ክርስትና በዚህ ከተማ ተጠናክሮ የቆመ ይመስላል። ነገር ግን አንድ ሰው በእነዚህ አብያተ-ክርስቲያናት ውስጥ የብሔረሰቦች አስተዋጽኦ ምን እንደሚመስል ለማወቅ ባደረገው ጥናት የቤተ-ክርስቲያን አባላት የአካባቢው ሰዎች እንዳልሆኑ ለማወቅ ችሏል። የአካባቢው ሁለት ብሔረሰቦች የሚገኙበት አንድ ትንሽ ቤተ-ክርስቲያን ቢኖርም ይህ ቤተ-ክርስቲያን እያደገ ሳይሆን እየመነመነ ሔዷል። ስለዚህም የከተማው የቤተ-ክርስቲያን እንቅስቃሴ ከብሔረሰብ አስተዋጽዖ አንጻር ጥናት እስኪደረግ ድረስ እንዲህ ዓይነቱ መረጃ ባለመኖሩ ሚሲዮናዊው ከላይ በሚያየው ብቻ ተታልሎ ነበር።

የቀጠለ....

# የከተማን የደም ሥሮች መረዳት ለወንጌል ተልዕኮ

<u>ማህበራዊ ቡድኖች</u>

በዚህ ጽሑፍ መጀመሪያ ላይ ከተማ እንደ ብዙ የወርቅ ማዕድን ስፍራ ተመስሎ ቀርቧል። አንዳንዶቹ የወርቅ ማዕድናት አሁን የተነጋገርንባቸው ብሔር ብሔረሰቦች ናቸው። እነዚህን በከተማው ላይ ከሰሜን ወደ ደቡብ እንደተዘረጉ ሥሮች ልንቆጥራቸው እንችላለን። ከዚህ በተጨማሪም ከምስራቅ ወደ ምዕራብ እንደተዘረጉ ሥሮች ሊቆጠሩ የሚችል ማህበራዊ ክፍሎች ወይም መደቦች ደግሞ አሉ።

በከተማ ወስጥ ከብሔረሰብ ክፍፍል ውጪ የተሰማሩበት ሙያ አንድ የሚያደርጋቸው የሙያ መደቦች አሉ። እነዚህ የሙያ ቡድኖች በማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ መሠላል ላይ ሲታዩ ከመሰላሉ የላይኛውና የታችኛው ክፍል አካባቢ የተሰባሰቡ ናቸው። የድርጅቶች ሥራ አስፈጻሚዎች፣ የፊልምና የቲያትር ተዋናዮች፣ በማኔጅመንት ደረጃ የሚገኙ የመንግስት ሠራተኞች፣ ባለ ከፍተኛ ማዕረግ የጦር አዛዦች፣ በብሔረሰብ ከሚደረግ መሳሳብ ውጪ ሆነው በደረጃቸው እርስ በእርሳቸው የተያያዙ ሊሆኑ ይችላሉ። በማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ ደረጃ የታችኛው ክፍል የሚገኙ ሴተኛ አዳሪዎች፣ አደንዛዥ ዕጽ አስተላላፊዎች፣ ለማኞች፣ ሌቦችና ቀማኞች የመሳሰሉት ከብሔራቸው ተለይተው ከኑሮ ደረጃ አንጻር እርስ በእርስ የሚያቀራርባቸው ነገር ይኖራል። እነዚህ ቡድኖች፣ ምንም እንኳን ሁሉም በክርስቶስ መዳን የሚያስፈልጋቸው ቢሆኑም፣ እያንዳንዳቸው የራሳቸው የሆነ ችግሮችና ፍላጎቶች ያሏቸው እንደመሆኑ የተለያየ የወንጌል ስርጭት ስልት መጠቀም ያስፈልገናል።

ከተሞች እንደ አንድ አካል

ከተሞች የወርቅ ማዕድን የሚወጣባቸው ቦታዎች ናቸው። ትልልቅ ብሔረሰቦች ያሉባቸው ናቸው። እንዲሁም ትልልቅ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ መደቦች ያሉባቸው ናቸው። እንደዚህ ያለው የተወሳሰበው ሁኔታ የተለያየ ዓይነት የወንጌል ስርጭት አሠራር እንድናስብ ያደርገናል። ከዚህ በተጨማሪም ሊታይ የሚገባ አንድ ሌላ ደረጃ አለ። ከተማ ያለማቋረጥ በእንቅስቃሴ ላይ ያለ ብዙ ክፍሎችን በውስጡ ያካተተ አንድ አካል ተደርጎም ይወሰዳል። እርስ በእርስ እንደተያያዙና እንደሚደጋገፉ የሰው አካል ብልቶች ናቸው።

በከተማ ውስጥ የሚኖሩ የተለያዩ የባለሙያ ቡድኖች እርስ በእርሳቸው የተያያዙና የተደጋገፉ ናቸው። እንደዚህ ዓይነቱ እርስ በእርስ የመያያዝ ሁኔታ የከተሞች ሕይወትን የሚያሳይ ዓይነተኛ ባህርይ ነው። መምህራን የሚያስፈልጋቸውን ጫማ ለማግኘት በጫማ አምራቾች ላይ ይደገፋሉ። እነዚህ ጫማ አምራቾችም መኪኖቻቸውን የሚጠግኑላቸው ሜካኒኮች ያስፈልጋቸዋል። ሜካኒኮች በተራቸው ለምግብ ፍላጎቶቻቸው በሆቴል ሠራተኞች ላይ ይደገፋሉ። የሆቴል ባለሙያዎችም ጤናቸው በታወከ ጊዜ የሚረዷቸው የጤና ባለሙያዎች ያስፈልጋሉ። የጤና ባለሙያዎችም በተመሳሳይ ከመንግስት የሥራ ፈቃድ ማግኘት አለባቸው። የመንግስት ቢሮዎችም እነዚህን ሁሉ ቢዝነሶች ለመከታተል ጸሐፊዎችና የኮምፒውተር ባለሙያዎች ያስፈልጓቸዋል። ወደድንም ጠላንም የከተማ ህይወት እርስ በእርሱ የተደጋገፈና የተያያዘ ነው።

አማኑኤል ገዛኸኝ
የወንጌል አስተማሪ ፣ ሚሽን ሞላይዘር
ጭማሪ ጽሑፍ ፦ ጢሞቲዎስ ሞንስማ

# በየቀኑ 8 ክርስቲያኖች እየሱስን ለመከተል ባደረጉት ውሳኔ ይገደዳሉ

ዛሬ ለመተኛት ጋደም በምንልበት ጊዜ፣ 8 ሰዎች ኢየሱስን ለመከተክ በመወሰናቸው ይሞታሉ።
ይህ ቁጥር በጣም ብዙ እና የሚያሳዝን ነው። በአለም አቀፍ የክርስቲኖች ስደት ላይየሚያተኩረውና በጣም ጥልቅ የምርምር ዘገባ ለሚያቀርበውኦፕን ዶርስ 2020 ወርልድ ወች ሊስት" ባደረግነው ጥናት በአመታዊው ሪፖርት ወቅት በእያንዳንዱ ቀን በወርልድ ወች ሊስት ከተቀመጡት የመጀመሪያዎቹ 50 ሀገራት ውስጥ ስምንት ክርስቲያኖች በእምነታቸው ምክንያት ይሰዋሉ። ይህ ቁጥር በእርግጥ ካለው እውነታ ያነሰ እንደሚሆን ከግምት ውስጥ ማስገባት አለብን። ምክንያቱም በተለይ እንደ ሰሜን ኮሪያ እና አፍጋኒስታን ያሉ ዝግ ሀገሮች ወይም እንደ ናይጄሪ እና ሊቢያ ያሉ ግጭቶች የተንሰራፋባቸው ቦታዎች ላይ ግድያዎች በድብቅ ይካሄዳሉ ወይም/እና ሪፖርት ሳይደረጉ ይቀራሉ። በሰሜን ኮርያ እስር ቤት ወይም በአፍጋኒስታን ሙስሊም ጎሳ ውስጥ ማንም የክርስቲያን መገደል አይዘግብም።ሆኖም ኦፕን ዶርስ በሺዎች የሚቆጠሩ አማኞችንና ስደተኞችን አነጋግሮ ክርስቲያኖች በእምነታቸው ምክንያት እንደሚገደሉ ማወቅ ችሏል።

እናም ብዙ ክርስቲያኖች ለረጅም ጊዜ የመሰረታዊ ፍላጎት እጦትና ከማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ እርዳታ መገለል ሳብያ ለግጭት ተጋላጭነታቸውበመጨመሩ ሳቢያ(ም/ት) ይሞታሉ።

በዚህ አመት ባጠቃላይ የክርስቲያን ሰማዕታት ቁጥር ከ4,305 (WWL 2019) ወደ 2,983(WWL 2020) ቀንሷል። ሆኖም፤ የዚህ ቁጥር መቀነስ ምክንያት ወደ ሪፖርቱ ይመጣል። በናይጄሪያ፤ በእምነታቸው ምክንያት የሚገደሉ ሰዎች ቁጥር ሪፖርት አናሳ ሆኖ የተመዘገበው የሙስሊም ፉላኒ ታጣቂዎች ስልታቸውን በከፊል በመቀየራቸው ነው። አክራሪዎቹ ላለፉት ጥቂት አመታት እንዳየናቸው አይነት የክርስቲኖችን ቤት እና ክርስቲያን ማህበረሰቡ ላይ ወረራ ከማድረግ ይልቅ በአፈና እና የመንገድ ላይ ግድያዎች ላይ ይበልጥ ትኩረት አድርገዋል።( ታጣቂዎቹ ሀሰተኛ የመንገድ ኬላ(ማቋሚያ)ያዘጋጃሉ። ከዚያም አውቶቡሶችን ወይም ሌሎች ተሽከርካሪዎችን እያስቆሙ ሙስሊሞችን ሙስሊም ካልሆኑት የሚለይ የሀይማኖት መታወቂያዎችን ያያሉ።) ምንም እንኳን ኦችን ዶርስ የብዙ ሰዎች ሞት እንዳልተመዘገበ ቢገምትም፣ ከግማሽ በላይ የሚሆኑት የተገደሉ ክርስቲያኖች እና ጥቃት የተደረገባቸው አብያተ ክርስቲያናት ከሰሀራ በታች ባሉ የአፍሪካ ሀገራት ውስጥ ይገኛሉ። በናይጄሪያ፣ ሴንትራል አፍሪካ ሪፐብሊክ በ (ሲ.ኤ.አር)፣በደቡብ ሱዳን፣ዴሞክራቲክ ሪፐብሊክ ኮንጎ እና ቡርኪናፋሶ ብቻ 2476 ክርስቲያኖችለእምነታቸው ሰማዕት ሆነዋል። 1350 በናይጄሪያ የተመዘገበ እና924 ደግሞ በ ሲ.ኤ.አር። በናይጄሪያ ክርስቲያኖች የፉላኒ ታጣቂዎች እና ቦኮሀራም፣አይ.ኤስ.ደብሊው.ኤ.፣ እና በርካታታጣቂ ወንጀለኞች ቡድን የክርስቲያን ማህበረሰቡን እና ቸርችን የሚያጠቁ፣የሚገሉ፣የሚያግቱ እና አስገድደው የሚደፍሩ ኢላማ(ትኩረት) ናቸው።

ለመጀመሪያ ጊዜ ቡርኪናፋሶ የመጀመሪያዎቹ 50 ውስጥ 28ተኛ ሆና ገብታለች። አልቃይዳ እና እስላማዊ መንግስት በሀገሪቱ ተጠናክረው መስፈራቸው ክርስቲያኖችን እንዲሁም መንግስትን እንዲያጠቁ አስችሏቸዋል። እ.ኤ.አ በ 2019፣ ቡርኪናፋሶ ውስጥ ቤተክርስቲያን በተደጋጋሚ በአምልኮ ሰአትና ከዐምልኮ ሰአት በኋላ (ኢላማ ስትሆንና) ስትጠቃ ይታያል። በአክራሪ ሀይሎች እምነታቸውን እንዲክዱ ወይም ራሳቸውን አሳልፈው ለሞት እንዲሰጡ ሲገደዱ ይታያል። የስደቱ አስከፊነት እና በእግዚአብሄር ህዝቦች ህይወት ውስጥ ያለው የእምነታቸው ሀያልነት ምስል ነው።
የተለያዩ የሀይማኖት ቡድኖች ያንሰራሩ በነበሩባት በአንድ ወቅት ሰላማዊ በነበረችው ሀገር ፅንፈኛ የእስልምና ታጣቂዎች የቤተክርስቲያን መሪዎችን ገድለዋል፤ የተለያዩ ቤተሰቦችንም በማገት ገንዘብ ጠይቀዋል፤ ቤተክርስቲያኖችንና ት/ት ቤቶችንም አቃጥለዋል። ካሜሮንም አስከፊ የስደት ሁኔታዎችን አስተናግዳለች።
በእነዚህ ሀገራት ያለው ሁከት ኦፕን ዶርስ"ከሰሀራ በታች ባሉ የአፍሪካ አካባቢዎች እየተስፋፋ ያለ በገንዘብ፣በመሳሪያዎች፣በመድሀኒት እና በተደራጀ ወንጀል የተደገፈ የእስልምና የተፅዕኖ ወጀብ" ብለው ለጠሩት መንገድ እያመቻቸ ነው። ህግጋት እና መንግስት ውጤታማ ባልሆኑባቸው ደካማ እና ያልተደራጁ ክልሎች ውስጥ ያሉ የክርስቲያን ማህበረሰቦች ያለ ጥበቃ ይቀራሉ።
በቅርቡ በዲሴምበር 28, 2019 የተለቀቀው የአስራ አንድ ናይጄራውያን ክርስቲያኖችን በ ኢስላሚክ ስቴት ዌስት አፍሪካን ፕሮቪንስ(ISWAP) መገደል የሚያሳየው ቪዲዮ አንድ ማስረጃ ያቀርባል። ይኸውም ISIS ከ አምስት አመታት በፊት 21 ክርስቲያን ወንዶችን በሊቢያ ዳርቻ ላይ ሲደርሱ የላኩት ያንኑ መልዕክት መድገም ነው። በሁለቱም ቪዲዮዎች ላይ ሰማዕታቱ ቡርትካናማ ልብስ ገዳዮቻቸው ደግሞ ጥቁር ልብስ ነበር የለበሱት። እስካሁን በ ISWAP ከተገደሉት ትልቁ ቡድን(ቁጥር) መሆኑ ተዘግቧል።

ዋና ጽሑፍ፦ ሊንዲ ሎውሪ ( የኦፕን ዶር አገልጋይ)
ትርጉም ፦ ህልዳና ብሩክ
ኮምፒውተር ጽሁፍ ፦ ሒወቴ ታደሰ

# ወንጌላዊ ራይን ሃርድ ቦንኬ
# አ ፕ ሪ ል 1 9 4 0 - ዲ ሴምበ ር 2 0 19

ታሪኩ የሚጀምረው የአዙዛው ጎዳና የወንጌል ንቅናቄ ላይ ነው ብዙዎች ምንን ከምን አገናኘህ ትሉኝ ይሆናል ግዴለም እኔም ልጻፍ እናንተም እያነበባችሁ ተከተሉኝ። ወንጌላዊው ታሪኩን እነዲህ ያወጋል አንድ ቀን የቤተሰቤን የዘር ሀረግ ለመመልከት ቤታችን ውስጥ ያሉ ምስሎችንን እና አንዳንድ መረጃዎችን ማገላበጥ ጀመርኩ አያቴም አባቴም የእግዚአብሔር ቤት አገልጋዮች መሆናቸው ቢያስደንቀኝ ወደ አባቴ ዞሬ እስኪ የቦንኬ የዘር ሀረግ ውስጥ እንዴት ክርስቶስ እንደገባ ንገረኝ አልኩት። እርሱም ታሪኩን እንዲህ ጀመረ ከመወለዴ አስራ ስምንተ አመት በፊት ወደ መንደራችን ስለመጣ ሊዊስ ግራፍ ስለተባለ ሰው ያወራኝ ጀመር ይህ ሰው የጀርመን ተወላጅ የነበር ቢሆነም በወጣትነቱ ተሰዶ አሜሪካን ሃገር ይኖር የነበር ነው፤ በዚያም በጠንካራ ሰራተኛነት እና በጠንካራ መርህ ባለሃብት እና የበለጸገ ሰው ሆነ። የሰራተኛነት ዘመኑ ሲያበቃ  በጡረተኛነት ዘመኑ ላይ ወደ ጀርመን በመንፈስ ቅዱስ ሃይል ተሞልቶእና በልሳን እየተናገረ ተመለሰ ።

ይህ የማወራው ንቅናቄ ፔንቴኮስታል ንቅናቄ ነው። በባዕለ ሃምሳ ቀን የተጀመረ በ1906 በሎስ አንጀለስ አዙዛ ጎዳና ላይ የቀጠለ አለምንም የደረሰ ንቅናቄ ነው። ወቅቱ 1922 ዓ.ም  ክረምት ነው፤ የሚያወጣው ድምጽ የጦር መኪናን የመሰለ አንድ ተሽከርካሪ በአቧራማው ጎዳና ላይ ይበራል። በዚህ በባልቲክ ባህር አቅራቢያ ባለው የጀርመን ክፍል ከሁለተኛው የዓለም ጦርነት በኃላ መኪና በአብዛኛው አይታይምና ሰዉ ይህን አቧራ እየረጨ የሚያልፈውን መኪና ቆም ብለው በአግራሞት ያዩታል።
አካባቢውን እየቃኘ ጉዞውን ቀጠለ የሁለተኛው የአለም ጦርነት ጀርመንን ብዙ አሳጥቷታል ከ3,000,000 በላይ ሰዎች በአራት አመት በዚህ ጦርነት አጥታለች፤ ከዚህም ባለፈ ግን የነበሯት መሰረተ ልማቶች ሁሉ ወድመዋል እንደሃገር ለመቀጠል የተንገዳገደችበት ወቅት ነበር። ሊውስ ግራፍ መንገዱን ቀጥሎ ወደ አንድ ብዙ ቤቶች ወደ ተከማቹበት መንደር ደረሰ ከሰፈሩ የሚወጣው መልካም የዳቦ መዓዛ የልጅነት ትውስታውን ቀስቅሶበታል ከዚህ ግን ባለፈ ለሱ በሃገሩ ከእምነት እና ቅዱስ ቃሉን ከመኖር ይልቅ ሰፍሮ የኖረው የሃይማኖተኝነት በሽታ ትልቅ ሃሳብ ነው። ውስጡ ባለው ጸጋ ለህዝቡ ብርሃንን ይዞ መምጣትን ናፍቋል።

ለረጅም ሰዓታት በጉዞ ላይ ነበርና በዚህች መንደር ከፍሎ ሊያድርበት የሚችልበት ቦታ ከዚያም ሲያልፍ በውስጡ ያለውን የክርስቶስ ወንጌል የሚያጋራባት ከተማ እንደሆነች ስለተሰማው በዚያ ለመቆየት አሰበ። በአንድ ዳቦ መጋገሪያ ፊትለፊት መኪናዋን አቆመ፣ የተወሰኑ የአካባቢው ሰዎች ይህን የሚያምር መኪና ይዞ ወደ መንደራቸው የመጣውን ሰው እና ውቧን መኪናውን ለማየት ከየሱቃቸውና መኖሪያቸው ብቅ ብቅ ማለት ጀመሩ። መኪናውን ካቆመበት ቦታ ጎን ካለው ዳቦ ቤት አንድ ራሰ በራ ሰው እጁ ላይ ያለውን ዱቄት የለበሰው ዩኑፎርም ላይ እየጠረገ ብቅ አለ። ለዚህ የዳቦ ቤት ባለቤትም እንደምን ዋልክ ሉዊስ ግራፍ እባላለው የክርስቶስ ወንጌል አገልጋይ ነኝ ብሎ ሰላምታ አቀረበ፤ ዳቦ ጋጋሪውም ጌራልድ እባላለው እኛ እዚ ሁላችንም ሉተራን ነን በማለት መለሰለት።
ሉተራን በጣም ጥሩ ነው ነገር ግን ሉተራንም ኢየሱስ ያስፈልጋቸዋል ብሎ መለሰለት፤ ቀጠለ እሚገርምህ እኔም ከሉተራን ቤተሰብ ነው የተገኘውት ነገር ግን ክርስቶስን አግኝቼ መንፈስ ቅዱስን ተቀብያለው አንተ መንፈስ ቅዱስን ተቀብለሃል ብሎ ጠየቀው። እርሱም ስለምትለው ነገር አላውቅም የሚል ምላሽ ሰጠው።

ይኸውልህ ወደ ኮኒስንበርግ ነበር እየተጓዝኩ የነበረው እንደማስበው መንገድ ስቻለው አሁን ያለሁት የት እንደሆነ ትነግረኛለህ የሚል ጥያቄ አቀረበ። ዳቦ ጋጋሪውም ትሩንዝብሎ መለሰለት።
ሉዊስም ይህን ቦታ ሰምቼው አላውቅም ነገር ግን እግዚአብሔር ወደዚህ ስፍራ የመራኝ ለምክኒያት ነው ወንጌልን ልናገር ምሪቱ ነው አለው። ዳቦ ጋጋሪውም መልሶ ነገርኩህ እኮ እኛ ሉተራኞች ነን አለው፤ ሉዊስ መልሶ ችግር የለም ለስብከቴ ልባችሁ እስኪከፈት ጠብቃለው ነገርግን እዚ ሰፈር የታመመ ሰው አለ ብሎ ጠየቀው ።



መከሩ ይቀጥላል እየሱስ ይጣል!! መንፈስ ቅዱስ የክርስቶስን ቃል ለመፈጸም ቆራጥ ነው። ( ቤተክርስቲያኔን እሰራለሁ ማቴ 16:18). ይህ የሱ ስራ ነው የእኛም ጭምር ነው ደግሞ። እግዚያብሔር የገነባውን ማንም ሊያፈርሰው አይችልም። እርሱ የከፈተውን በር ማንም ሊዘጋ አይችልም የክርስቶስ መስቀል የሰው ልጅ በሚያመጣው በየትኛውም የሚያጓራ የውቂያኖስ መናወጥ ድምጽ የማይነቃነቅ አለት ነው። ሃይማኖት የለሽ እና ከሃዲዎች እግዚያብሔር የለም እና ሞቷል ብለው ለፍፈው ነበር እነርሱ የክርስቶስ መቃብር ላይ መልካም ሞት የሚል ጽሑፍ ለማጻፍ ሲሞክሩ ክንዳቸው ላይ ግን አንድ እጅ አረፈች አንድ ድምጽም እንዲ አለ ፡- ሞቼም ነበርሁ እነሆም፥ ከዘላለም እስከ ዘላለም ድረስ ሕያው ነኝ፥ የሞትና የሲኦልም መክፈቻ አለኝ (ራዕይ 1፡ 18) ።



እኛ ከኃላ የመጣን ነን ፤ የማብሰሪያው እሳት ከጀግኖች፣ ከሰማዕታት እና ከማይታወቅ ሚሊዬኖች አማኞች ። ለእኛ ምስክር እና ብርታት ለመሆን በክብር እንደደመና ከብበው ያዩናል። ምናልባት የመጨረሻውን ዙር ለመሮጥ ድርሻው የኛ ሊሆን ይችላል እንግዲህ በእየሱስ ስም እናድርገው!!



ለሮበርት ሊያርዶን የእግዚአብሔር ጀነራሎች ሚሲዬናውያኖቹ መፀሐፍ መግቢያ ላይ ቦንኬ ከጻፈው የተተረጎመ ይህ የወንጌል አርበኛ ዛሬ ሩጫውን ጨርሷል የክብርም አክሊል በሰማይ ይጠብቀዋል። እንደተናገረው ለእኛ ምስክር እና ብርታት ሆነው ከከበቡን የእምነት አባቶች አንዱ ሊሆን ሩጫውን ጨረሰ። ይህ የዕምነት ጀግና እንዲህ ይላል እግዚአብሔር ሁልግዜ ከሰራተኞች ጋር ይሰራል፣ ከተጓዦች ጋር ይጓዛል ግን ከተቀማጮች ጋር ግን መቼም አይቀመጥም።
የማይቆሙ ሁሌ የሚሄዱ ሰራተኞች የሆኑ የክርስቶስ ስም በህዝቦች ሁሉ ዘንድ ይታወቅ ዘንድ የቆረጡ የዘመናችንን ቦንኬዎች እግዚአብሔር እነዲያስነሳ መሻቴ ነው።
"ቀድሞ ወንዝ በወረደበት ቦታ ሁሉ ወንጌልህ እንደገና ይፍሰስ" ሉተር ዊሻርድ



ምነጭ ፡- ኢቪንግ ኤ ላይፍ ኦፍ ፋየር
- ጋድስ ጀነራል ዘ ሚሽነሪስ
- የዊኪፒዲያ ድህረ ገጽ
- ክርስት ፎር ኦል ኔሽንስ ድህረ ገጽ

ትርጉም ፡ አማኑኤል ገዛኸኝ

## ወንጌላዊ ራይን ሃርድ ቦንኬ
## አ ፕ ሪ ል 1 9 4 0 - ዲ ሴምበ ር 2 0 19



ዳቦ ጋጋሪውም ሐኪም ነህ እንዴ !ብሎ ጠየቀው ሉዊስም አይደለሁም ነገር ግን ታላቁን ሃኪም እወክላለው። አንድ ጥያቄ ልጠይቅህ እዚህ የታመመ ሰው ካለ እና እኔ ጸልዬላቸው ከተፈወሱ እግዚአብሔር እኔን ለእናንተ ወንጌልን እንደሰብ እንደላከኝ ታምናላችሁ? ስብከቴንስ ትሰማላችሁ ብሎ ለጋጋሪው ጥያቄን አቀረበ ጋጋሪውም ከፈገግታ ጋር አናቱን እየነቀነቀ አዎ የሚል መላሽ ሰጠ።



ይህ ጋጋሪ ሉዊስ የማያውቀው በትሩንዝ ያለ እያንዳንዱ ነዋሪ ግን የሚያውቀው አንድ በጠና የታመመ ሰው ትዝ አለው ከዚህ ትዝታ ጀርባ ይህ መጤ ሰውዬ ጸሎቱ አልሰራ ብሎ በመሸማቀቅ ወደ መጣበት ሲመለስ በልቡ ተሳለ ቀጠለም አዎ እዚ በጣም የታመመ ሰው አለ ብሎ በመንደሩ ወደሚታዩት የመጨረሻ ቤቶች እጁን ጠቆመው ወደዚያም ጠጋ ሲሉ በጣም ከፍተኛ ጩኸት ይሰሙ ጀመር ። ሊዊስ የመጀመሪያ ወደ ልቡ የመጣው ሃሳብ መኪናውን አስነስቶ ከዚያ አካባቢ መጥፋት ነበር ነገር ግን ልቡ እንዳይደነግጥ እራሱን ጠንከር አደረገ ለጋጋሪውም ማን ነው የሚል ጥያቄ አቀረበ፤ ጋጋሪውም ኦገስቲን ቦንኬ ይባላል እዚህ ከተማ ላይ በጣም ባለጠጋ እና የእነዚህ ዳቦ ቤቶች ባለቤት ነበር ምን ያደርጋል ባልታወቀ በሽታ ይኸው ይሰቃያል፣ ዶክተሮችም መፍትሄ ሊጡተር አልቻሉም ቀን ከሌሊት ጩኸጡ በሰፈሩ መሰማት ከጀመረ አመታት ተቆጠሩ አለው። አሁን ላይ ሉዊስ የዚህ ሰው ጩኸት በታላቅ ርህራሄ ውስጥ ሆኖ ሰማው ፣ ይህ በሰይጣን እስራት ውስጥ የነበር ሰው ጩኸት ነው።



ሉዊስ ወደ ጋጋሪው ዞር አለና ለዚህ ሰው ልጸልይለት እወዳለው ቤተሰዎቹ ይህን እንዳደርግ ይፈቅዱልኝ ይመስልሃል ብሎ ጠየቀው። ጋጋሪውም በዳቦ ቤቱ ፊትለፊት የቆችውን የሉዊዝ መኪና እየተዟዟረ ይመለከት የነበረውን ወጣት ሄርማን ና ወደዚህ ብሎ ጠራው ወጣቱም ወደ እነርሱ አመራ ይኸውል ለአባትህ አንድ ሰባኪ ለጸሎት ሊመጣ ነው ብለህ ንገር አለው።



ጋጋሪው ግን አንዴ መለስ ብሎ ምን አይነት ሰባኪ መጥቷል እንበለው ማለቴም ሉተራን፣ ካቶሊክ ወይስ ወንጌላውያን ? ሉዊዝም መለስ ብሎ ስለ አዙዛ ጎዳና ሰምታችኋል፣ አሜሪካን ሃገር ስለነበረው መነቃቃትስ፣ ሎስአንጀለስ ስለነበረው ? ወጣቱም ዳቦ ጋጋሪውም አናታቸውን አናውቅም በማለት ነቀነቁ። ችግር የለም ለኸር ቦንኬ አንዲ በሉት በመንፈስ ቅዱስ ሃይል የተሞላ ሰው ነኝ ብሎሃል በሉት። እኔ ስጸልይለት ማንም ቄስ እንደጸለየለት አይሆንም፣ ሰውነቱም ፈጽሞ ይድናል ብሏል በሉት አላቸው።
ጋጋሪውም ወደ ወጣቱ ልጅ ዞር ብሎ በልሂድ ለአባትህ ይህን ንገር ብሎ ላከው። ወጣቱም በፍጥነት ሳይክሉን እያሽከረከረ ወደ ቤቱ ሄደ።

ይህ ሳይክል እየነዳ የሄደው ሄርማን ቦንኬ ነበር አባቴ በግዜው ገና 17 ዓመቱ ነበር። በጠና የታመመው ደግሞ አያቴ አውገስቲን ቦንኬ ነበር።

የቦንኬ የዘር ሃረግ በተገለለች ኦስተርፕሩሰን በተባለ የጀርመን ግዛት ወይም ምስራቅ ፐርሺያ ይኖር ነበር። የእኛ አካባቢ በአለም አቀፍ ስምምነት በአንደኛው የአለም ጦርነት ማብቂያ ላይ የፈጠረች ቦታ ነበረች፤ ከተቀረው ጀርመን የተነጠለ ስፍራ ነበር የባለቲክ ሃገራት እና በምሰራቅ ደግሞ ከራሽያ ጋር ትዋሰናለች። በዚህ በተገለለ፣ ቀዝቃዛ እና በተረሳ ስፍራ በ1922ዓ.ም የመንፈስ ቅዱስ ሃይል ነእኔ እና ለዘሬ ብርሃን ሊሆን ፈነጠቀ ይህንን ብርሃን ደግሞ ሉዊስ ግራፍ ይዞልን መጣ ህይወቴንም ተቆጣጠረ።

ሉዊስ ግራፍ ወደ አያቴ አውገስቲን ቦንኬ ቤት ዘለቀ። በክፍል ውስጥም የክርስቶስን ሃይል ይጠራ ጀመር፣ መንፈስ ቅዱስ ነገሮችን እንደ አዲስ እንደሚሰራ፣ የታመመውን እንደሚፈውስ፣ የሞተን እንደሚያስነሳ ማወጅ ጀመረ። አልጋ ላይ የተኛ የነበረውንም እጁን ይዞ እንዲነሳ እና በክርስቶስ ሃይ መፈወሱን እንጂያውጅ ተናገረበት። አያቴም የሰማይን ሃይል በሰውነቱ ተሰማው፣ በሽተኛ ሆኖ ከነበረበት አልጋ ላይ ተነሳ፣ በክፍል ውስጥ መንቀሳቀስ፣ መሮጥ እነ መዝለል ጀመረ። ህመም ይሰማው የነበሩ የሰውነት ክፍሎቹ በረቱ፣ ጉልበቱ ሲታደስ
ተሰማው ታሞ በተኛበት አልጋው አጠገብ ለአመታት አብረው የተሰቃየችው ባለቤቱ ማሪ ማልቀስ ጀመረች ለመረዳት እና ለማስረዳት ከባድ ቢሆንም ነገሩ ግን እጅግ ድንቅ ነበር። ሉዊዝ ግራልፍ ለአያቶቼ ጌታን እንዲቀበሉ ንሰሃ አስገባቸው እጅም ጭኖ ጸለያላቸው መንፈስቅዱስንም ተሞሉ።
ክርስቶስ ወደ ቦንኬ ዘር በዚች ድንቅ ታሪክ ነበር የገባው ከትውልድ ትውልድ ልናመልከው ልንከተለው ያሸነፈን ዘራችንን የወረሰው። በዚህ የታሪክ ሒደት በሞቀ እና በደስታ በተሚላ እግዚአብሔርን ወዳድ በሆነ ቤተሰብ የታሪክ ሌላኛው መልክ እና ገጽታ ሊታይ እውን ሆነ።
ሰላም እና ደህንነቱ የተጠበቀ ኑሮ በቅስፈት ግን ይህ ተቀይሮ በግርግር፣ ድንጋጤ፣ ፍርሃት እና ጭንቀት የተሞላ ኑሮ 1945 እ.አ.አ በምስራቅ ፕርሺያ ስታልባክ የተባለ ቦታ። የሁለተኛው የአለም ጦርነት የማብቂያ ወቅት ነበር የአዶልፍ ሒትለርም ጦር እፈራረሰ እና የመጨረሻው የሽንፈት ጽዋውን ሊከናነብ በደጅ ነበር።

የተመቸ የልጅነት ቆይታዬ በጣም አስደንጋጭ እና አስፈሪ ድምጽ በሚያወጡ ከባድ መሳሪያዎች፣ ቦንቦች እና የጀት ውጊያዎች የተናጋበት ወቅት ነበር ። ምን እደተቀየረ አልገባኝም ነበር ወደ መስኮቱ ሮጬ ምን እየተፈጠረ እንደሆነ ለመመልከት ሞከርኩ ። ያ ጨለማው ምሽት በሚነዱ ህንጻዎች እና ፍንዳታዎች ብርሃኑን አግኝቷል። ለእኔ አይነቱ
5 ዓመት ልጅ ቤታችን ካለው የእሳት መሞቂያ ስር እንደሚታየው እሳት ነው ከዚያ ያለፈ ትርጉም ላይኖረው ይችላል። ልክ እንደ ሻማ እሳት ይህ ነው የማይባል ጉዳት እንደማያደርሰው ማለት ነው።

እናቴ ሜታ ልጆቿን ስድስታችንንም በእሳት መሞቂያው አጠገብ ሰብስባን መጸለይ ጀመረች። እኔ ከወንድሜ ማርቲን ስር ሸጉጥ አልኩ። ድንገት የቤታችን በር በሃይል ተከፈተ ሁላችን ደነገጥን በሩ ላይ አንድ ወታደር ቆሟል፤ ይህ ወታደርም በአባታችን ሄርማን ቦንኬ የተላከ ወታደር ነበር። "እስካሁን እዚህ ምን ትሰሪያለሽ ሜታ "! በጩኸት ተናገራት ። አሁን ራሱ እነዚህን ሁላ ልጅ ይዘሽ ለመውጣት ዘግይተሽ ይሆናል አሁን በፍጥነት ከዚህ ስፍራ አምልጡ አላት ።

እናቴም እሺ እንዳልክ እናደርጋለን ለሔርማንም ንገረው ብላ እዛው እሳት ዳር እንደተሰበሰብን ጸለይን። የአሰቃቂ፣ ከባድ፣ የተስፋ መቁረጥ፣ ከሞት ጋር የመታገል፣ የተስፋ እና የረጅም አሰልቺ ኑሮ ጅማሬ ምሽት ሆነች።

እናቴ እኛን ይዛ ከጎረቤቶቿ ጋር ነፍስን የማዳን ያለመሞት የመትረፍ ረጅም ጉዞ ጀመረች ከከተማችን በከባድ የጦር ቀጠናዎች አልፈን ወደ አያቶቻችን ሃገር ወደ ዳንጊዝ ከዛም በባህር ወደ ዴንማርክ አቀናን እዛ ስንደርስ ስደተኛ ጦርነት አምልጦ የመጣ ነበርና ሁሉም በእንክብካቤ ተቀብሎን ነበር። ነገር ግን ጀርመን ጦርነቱን ተሸንፋ ሒትለር በአይሁዶች ላይ ያደረሰው በደል እና ሌሎች አሰቃቂ ታሪኮች ለዓለም አቀፉ ማህበረሰብ ይፋ መሆን ሲጀምሩ እነዛ ደጋግ እጆች በቁጣ ይለወጡ ጀመር ስለሆነም የዴንማርክ መንግስት ስደተኛዎችን ሁሉ አንስቶን በአንድ ካምፕ ውስጥ አጎረን ሌላ የሰቆቃ እና ከባድ አመታትን በዚያ አሳለፍን። በዚያ አምስት አመታትን አሳለፍን እኔ 9 አመት ሲሞላኝ ነበር ነገሮች ተለውጠው ወደ ሃገራችን ለመመለስ የቻነው ወደ ሃገር ቤት ስንመለስ አባቴ ከጦር ምርኮኛነት በምህረት ተለቆ ስራ ጀምሮ ነገር ግን በውስጡ የወንጌል ጥሪ አሸንፎት አገልጋይ ሆኖ ነበር የተገኘኘነው። የአባቴ አገልጋይ መሆን እኔን በብዙ ቀርጾኛል። ሁሌም ባይሆን እርሱ ወደሚያገለግልበት ስፍራ ይዞኝ ይሄዳል አንድ ቀን ግል ልዩ የሆነ ነገር ተፈጠረመንፈስ ቅዱስን ተሞላው አዲስ የሆነልምምድ ጀመርኩ። እይታዎቼ በብዙ ተቀየሩ ።

በመንፈሳዊ ህይወቱ እያደገ ይበልጥ የዚህ ጌታ ፍቅር እያሸነፈው፣ መንፈሳዊ ልምምዶች በእርሱ ላይ እየተገለጡ ይመጡ ጀመር፤ ከዛም ይበልጥ በእግዚአብሄር መንግስት ውስጥ ለመሳተፍ እና ብቁ የወንጌሉ ሰራተኛ ለመሆን መንፈሳዊ ትምህርት ለመማር ከጀርመን ፈረንሳይ፣ ከዛም በመርከብ እንግሊዝ፣ ከዛም በባቡር ወደ ለንደን፣ ከለንደንም ወደ ዌልስ አቅንቶ ባይብል ኮሌጅ ኦፍ ዋልስ መንፈሳዊ ትምህርቱን አጠናቀቀ። ሰፊውን የአፍሪካ አገልግሎቱ ከመጀመሩ በፊት በጀርመን በመጋቢነት ለሰባት አመት አገልግሏል። አስደናቂው የአፍሪካ አገልግሎቱም ከዚህ በኃላ በ1967 እ.አ.አ በሌሴቶ የጀመረ ነበር።

ቦንኬ እና ባለቤቱ አኒ በሌሴቶ ሰባት አመታትን በተለመደው መልኩ የሚሲዮናዊነትን ስራ እየሰሩ ቆይተው ነበር ቢሆንም ወንጌልን የማድረስ ትልቅ ሸክም ክንፍ እየዘረጋ ለመብረር እየተዘጋጀ ነበር። በእነዚያ ወቅት ነበር እግዚአብሔር ለቦንኬ አንድ ራዕያ ሳያየው ራዕዩ እንዲህ ነበር አፍሪካ በደም ስትጣጠብ ያየው ቦንኬ ይህንንም ራዕይ ከዚያን ግዜ አንስቶ ይናገረው እና ይኖረው ጀመር።

በእ.አ.አ በ1974ዓ.ም ዛሬም ድረስ ያለው ክራይስት ፎር ኦል ኔሽን የተባለው ወንጌልን ለዓም ማድረስን ዓለማው ያደረገው አገልግሎት ተጀመረ። ከዚህ አገልግሎት ጋር የቆመ አንድ ትሽ ህብረት ነበር። በቦትስዋና የወንጌል ፕሮግራሞቹ መካሄድ ጀመረው ጥቂት መቶ ሰዎች ብቻ መምጣታቸው በቦንኬ ውስጥ ሃዘንን ፈጥረው ነበር፤ ነገር ግን ቦንኬ በእነዚያ ስብሰባዎች መቶ ሺዎች እንደተሰበሰቡ አድርጎ መስበክ እና ማገልገል ቀጠለ በአስደናቂ ሁኔታም አንድ ሰው ከጉባኤው መሃል መዝለል እናመጮህ ጀመረ ተፈወስኩ! ተፈወስኩ! እያለ ጉደ,ባኤውን በጩኸት ናጠው፣ ሌሎች አምስት ሰዎችም በዚያ ቀን ተፈውሰው ከፍተኛ ደስታ ሆነ።

በዚያ ስፍራ ድንቅና ተዓምራት እየሆነ ሰዎች እየተፈወሱም መሆኑ በከተማው በፍጥነት ተስፋፋ፤ በዚያች አጭር የአገልግሎት ግዜም ቦንኬ ስታዲየም የሞሉ ሰዎችን ማገልገል ጀመረ ሺዎች ክርስቶስ ኢየሱስን በማመን የሐጢያት ስርየት ለማግኘት ጥሪ ሲያቀርብ ወደ ፊት ይጎርፉ ጀመር፣ ሺ ዎች ተፈውሰው ከደዌ እና እስራት ይፈቱ ጀመር ይህ ሁሉ ግን የብዙ አስደናቂ ታሪኮች ጅማሬ ሆነ ። ቦርኬ ወደ ቦትስዋና ለጉብኝት ሲመለስ በዚያ ሃገር ትልቁ ቤተ ዕምነት መሪ እንዲህ ሲል አወራው ስምንት ፐርሰንት የቤተዕመነቱ መጋቢዎች በዚያ የመጀመሪያው ጋቦሮኔ ላይ የነበረው ክሩሴድ ፍሬዎች እንደሆኑ አበሰረው።

ቦንኬ አገልግሎቱን የጀመረው በድንኳን ውስጥ ሲሆን እስከ 34,000 ሰዎች ይይዝ ነበር፤ ይህ ድንኳን ግን በከፍተኛ ንፋስ ወድሞ አንድ ትልቅ ኮንፍራን ልካሄድ ከታሰበበት አንድ ቀን ቀድሞ በአውሎ ንፋስ መ፣ፍረስ አጋጠመው ቦንኬም አገልግሎቱን ሳይሰርዝ በውጭ ማገልገል ጀመረ ይህ አገልግሎት እንደውም ይበልጥ አድጎ እስከ 100,000 ሰዎች የተሳተፉበት ታላቅ ኮንፍራንስ ሆነ።


በአለማችን 7ቱንም አህጉራት በጠቃለለው አገልግሎቱ ወንጌላዊ ራይን ሃርድ ቦንኬ 79 ሚሊዮን ሰዎች በእርሱ አገልግሎት ወደ እግዚአብሄር መንግስት እንደተጨመሩ መረጃዎች ይናገራሉ።የዚህን ድንቅ ወንጌላዊ አገ፤ግሎት ለመካፈል በናይጄሪያ በአንድ ፕሮግራም 1.7 ሚሊዮን ሰዎች ተሰብስበዋል ይህ ታሪካ አይደለም የእግዚአብሔር አስደናቂ እጅ ማያሳ እንጂ።

ራይንሃርድ ቦንኬ በ2013 አንድ ቃለ መጠይቅ ላይ ሲናገር "አንዳንድ ሰዎች እኔ የፈውስ ወንጌላዊ እንደሆንኩ ይናገራሉ እኔ በሱ ደስተኛ አይደለሁም፤ እኔ እራሴን እንደ ደህንነት ወንጌላዊ ለታመሙት ግን እንደሚጸልይ አግልጋይ ነው ምመለከተው። በምንሄድባቸው ቦታዎች ሁሉ 98% ወንጌሉን በመስበክ ነው ጌዜ ምነወስደው"።

ቦንኬ 40 መንፈሳዊ መጽሐፎችን የጻፈ ሲሆን በ2009 ደግሞ የህይወት ታሪኩን ሊቪንግ ዘ ላይፍ ኦፍ ፋየር የተሰኘውን መጸሐፉን ለንባብ አውሏል ። ራይን ሃርድ ቦንኬ ከብዙ አገልጋዮች ሚለየው ከአገልግሎቱ ዘመኑ ማብቂ አስቀድሞ በብዙ ጸሎት እና የመንፈስ ቅዱስ ምሪት አገልግሎቱን ለወጣት ወንጌላዊው ዳንኤል ኮሌንዳ አስረክቦ በማሳደግ፣ በማብቃት፣ አብሮ በማገልገል እና እርሱ ሲያገለግል በመማከር እና መንገድ በማሳየት ትልቅ ትምህርት ለብዚዎች አስተላልፏል። ክራይስ ፎር ኦል ኔሽንስ አገልግሎት ዛሬም በዓለማችን በተለያዩ አህጉራት የወንጌሉን ስራ እየራ ሲሆን የራይን ሃርድ ቦንኬ ተተኪ ዳንኤል ኮሌንዳ ወንጌልን በሃይል እና በስልጣን እያገለገ ይገኛል።

ቦንኬ ካስተላለፋቸው የመጨረሻ መልዕክቶቹ አንዱ ለእግዚአብሔር ጀነራሎች ሚሲዮናውያኑ መጸሐፍ መግቢያ የጻፈው ጽሑፍ ይገኝበታል እርሱን እንድታነቡት እየጋበዝኩ ትራካውን ላብቃ::

በ1986 ምስራቅ አፍሪካ ማላዊ ሀገር ውስጥ ባለንቲር በምትባል ግዛት ውስጥ ወንጌል ክሩሴድ ተዘጋጅቶን በር። ባለንቲር ከስኮትላንዳዊው አስደናቂ የወንጌል ጀግና ዴቪድ ሊቪንግስተን በተወለደባት ከተማ ስያሜዋን ያገኘች ከተማ ናት። ዴቪድ ሊቪንግስተን በዚያ ስፍራ የሚሽን አገልግሎት የጀመረ እና ቤተክርስቲያን ተክሎ ያቺ ቤተክርስቲያን ማህበረሰብ፣ አድጋ ከተማ ሆና ዛሬ 60,000 ሰዎች ሚኖሩባት የማላዊ ብዙ ቁጥር ሚኖርባት ከተማን መመስረት የቻለ ሰው ነበር። ሊቪንግስተን ከመሞቱ በፊት በሱ አገልግሎት አምኖ የዳነ አንድ ሰው ብቻ እንደሆነ ያስብ ነበር ከማስታወሻው የጻፈውን ልጥቀስ :- እኛ ልክ በምድረበዳ እንደሚጮህ ድምጾች ነን ለአስደናቂ እና ተዓምራዊ ነገዎች መንገዶችን የምንጠርግ። የነገዎቹ ሚሲዬናውያን በብዙ ወደ እግዚአብሔር መንግስት በሚጨመሩ እልፍ ቁጥር ባላቸው አዳዲስ አማኞች ይባረካሉ፣ ይሸለማሉም። እኛ የእነርሱ ፊታውራሪዎች እና አጋዦች ነን ።



እነርሱም ይህን አይዘንጉ ምንም ሚታይ በሌለበት የስኬት ተስፋ በማይታሰብበት ወቅት በእምነት የጠረጉ፣ ያረሱ እና የዘሩ አባቶቻቸውን እና ኃለኞቻቸውን አይዘንጉ። ያለጥርጥር ከእኛ በላይ ብርሃንን ያያሉ ነገር ግን እኛም ያለእረፍት አምላካችንን እናገለግላለን እነርሱም እንደሚሰብኩት ወንጌልን እስከመጨረሻው እንሰብካለን።



ሊቪንግስተን በ1873 ዓ.ም ወደ አምላኩ ሄዷል። እኛ በማላዊ በሊቪንግስተን ከተማ ከመቶ አመት በኃላ ነበር የሄድነው። የሊቪንግስተን ትንቢታዊ ቃሎችስ? ዝም በለው የተስፋ ቃሎች ብቻ ነበሩ? ተስፈኛ አስተሳሰቦችስ ብቻ ነበሩ? ያየነውን ነገር ልነግራቹ ደስተኛ ነኝ ። ከረጅም አመታት በፊት የተዘራው ዘር ዛሬ ፍሬውን እየሰጠ ነው። ለምሳሌ በአንድ ስብሰባ ( ክሩሴድ ) 150,000 ሰዎች ሲሳተፉ አይተናል። የማላዊ ሰዎች ያንኑ ወንጌል ሰምተዋል በዛ ለ16 ቀናት ነበርን እና በአስር ሺዎች የሚቆጠሩ ሰዎች ለሊቪንግስተን መልዕክት እኛ ለሰብክነው ምላሽ ሰጡ እኛም ለእርሱ እና ለኢየሰስ ሰበክንላቸው። በመላው ማለዊ ንቅናቄ ሆነ ፣ከባድ የሆነ የወንጌል እሳት ነደደ፣ መንፈስ ቅዱስ ለልቤ እንዲህ ሲል ተናገረኝ አሁን እየተራመድክ ያለኸው በቀድሞ ትውልድ እንባ ላይ ነው።



ድንገት እየሆነ ያለውን ሁሉ አየውት ። በእግዚአብሔር አንድ በሆነ አስደናቂ ቀድሞውን እና የወደፊቱን በሚያያይዝ የወንጌል ንቅናቄ ውስጥ ነበርን። ሁላችንም አንድ ነን ለአንድ ቡድንም አባላት ነን የቀደሙትም አካላችን ናቸው። እኛ በደስታ ከእኛ በፊት እነሱ የዘሩትን እያጨድን ነው። እኛ እያጨድን ያለነው ከእኛ ቀድመው ከሄዱት የተሻልን ስለሆንን አይደለም ለማጨድ ግዜው ስለደረሰ ብቻ ነው።
የሚያጭድ ደመወዝን ይቀበላል፥ የሚዘራና የሚያጭድም አብረው ደስ እንዲላቸው ለዘላለም ሕይወት ፍሬን ይሰበስባል። አንዱ ይዘራል አንዱም ያጭዳል የሚለው ቃል በዚህ እውነት ሆኖአልና። እኔም እናንተ ልደከማችሁበትን ታጭዱ ዘንድ ሰደድኋችሁ፤ ሌሎች ደከሙ እናንተም በድካማቸው ገባችሁ። (ዩሐ ወ 4:36 – 39) ይህ የማጨድ ግዜ ነው እመኑኝ!! የዓለማእን ህዝቦች በብዙ ተባዝተዋል። እድሎቻችንን በጣም ሰፋፊ፣ አስደሳች ናቸው። እኔ እናንተና ሁላችን ደግሞ እድለኞች ነን ይህንን ፍሬ ለማጨድ ይህ እድል የደረሰን ። ይህን ማወቅ ይኖርብናል የዘሩትን ልናከስር
አይገባም በዚህ ታላቅ ሃላፊነት ታምነናልና። ስለነሱ ስንል ልንጸና ልንታገል እከመጨረሻው መልካም አጫጅ እና ገበሬ ልንሆን ይገባል። ኤልያስ፣ ጳውሎስ፣ የጀስቲን ሰማዕታት እና ሊቪንግስቶን ስለወደፊቱ እኛ ላይ ነው ተስፋቸውን የጣሉት ። እነርሱ የከፈሉትንዋጋ እና መስዕዋትነት እንደ እድል ተጠቅመን ፍሬውን እንድንሰበስብ ይጠብቃሉ እኛ ደግሞ በዚህ አገልግሎት ልንኮራ ሳይሆን እድለኝነት ነው ሊሰማን የሚገባው።



በማላዊ የነበረን አገልግሎት ሁሉን እይታዬን ቀየረው ምን ያህል የእግዚአብሔር ሰዎች እና አግልግሎታቸው ከእኛ ጋር እንደሚገናኝ አስተዋልኩ። የዋህ የሆኑ አገልጋዬች፣ ሚሲዬናውያን፣ እረኛች ደግሞም አገልግሎታቸው እንደ ውድቀት ሚቆጠሩት ሁሉ የዚህ የትልቁ ምስል አካላት ናቸው ስለዚህም በመከሩ ፍሬ ደስታ ላይ ከእኛ ጋር አብረው ይሰለፋሉ።

# የአርጎባ ህዝብ ክፍል በኢትዮጵያ

**የሕዝቡ ቁጥር- 206,000**
**ዋና ቋንቋ- አርጎባ**
**የሕዝቡ ዋነኛ ሃይማኖት - እስልምና (95.40%)**
**ክርስትና ተከታዮች ከ ህዝቡ በ % ሲሰላ - 4.60%**
**የወንጌል አማኞች ከ ህዝቡ በ % ሲሰላ - 1.40%**

**ታሪክ**

አርጎባ ከሴማዊ ቋንቋ ተናጋሪ ሕዝቦች መካከል አንዱ ናቸው። ቋንቋቸውም የደቡብ ሴማዊ ቋንቋ ተናጋሪ ቡድኖች የሚመደብ ነው ። የዚህ ህዝብ አመጣጥ ሦስት የተለያዩ ታሪኮች እንደሆነ የሚጠቁሙ በአርጎባ አካባቢዎች የሚኖሩ እውቀት ባካበቱ ሽማግሌዎች የቀረበ መረጃ መኖራቸውን ያሳያል ። የመጀመሪያው ታሪክ የያዘው ከ800 ዓመታት በፊት "በነው እመያ" ተብሎ የሚጠራው የአረብ ነገድ ግዛቱንና ስልጣኑን በሌላ ጎሳ ሲያጡ እና ወደ ዓለም ሁሉ ሲበተኑ ነው ። ሁለተኛው ታሪክ በነቢዩ መሐመድና በሌሎች ሃይማኖት ተከታዮች መካከል ጠብ ሲነሳ ፣ ሰማኒያ ሁለት የሚያህሉ የነቢዩ ተከታዮች እስልምናን እንዲቀበሉ የሚጠይቀውን ደብዳቤ ይዘው ወደ ኢትዮጵያ ወደ አህመድ ነጃሽ መጡ ። ደብዳቤውን ካደረሱ በኋላ ወደ ይፋት በመምጣት እዚያ መኖር ጀመሩ ። በአርጎባ አመጣጥ ላይ ያለው ሦስተኛው ታሪክ ከቀደሙት ሁለት ይለያል ። በዚህ ታሪክ መሠረት አርጎባ ስደተኞች አይደሉም ግን ከአረቢያ ከመጡት የሃይማኖት መሪዎች በጣም ቀደም ብለው እስልምናን የተቀበሉ የጥንት እና የአገሬው ተወላጆች ናቸው ። ሽማግሌዎች የአርጎባን ከአገሪቱ መሃል ማዕከል ወደ ተለያዩ ክልሎች ለመሰደድ የተለያዩ ምክንያቶችን ይሰጣሉ ። ከሚጠቅሷቸው ዋና ዋና ምክንያቶች መካከል ንጉሠ ነገሥት ዮሃንስ ወደ ክርስትና አምነት እንዲቀየሩ ያደረገው ግዳጅ ፣ በልጅ ኢያሱ ዘመን የተፈጠረባቸው ችግሮች እና በራስ አበበ ወታደሮችና በፋሺስቶች ሥራ ናቸው። በእነዚህ ጊዜያት ውስጥ ፍልሰቶች እንደተከናወኑ ያረጋግጣሉ ። የተደረጉትን እንቅስቃሴዎች እና ለመስፈር የመረጡትን ቦታ ስናይ አርጎባዎች በደንብ ውሀ ለማጠጣትና ለእርሻ ያጸዱትን ተራራማ አከባቢዎችን እንደመረጡ እናያለን ። አንዴ ከተቋቋሙ በኋላ በግብርና እና በሽመና ሥራ ይሰማራሉ። ሽማግሌዎቻቸው ጉዳዩን እንደዚህ ያብራሩ ሲሆን ስለ መንደሮቻቸው ያላቸውን መረጃ ከመስክ ምልከታ ማረጋገጥ ተችሏል ። አርጎባ ለሁለቱም ለብሄረሰቦቹ እና ለቋንቋ የሚውል ስም ነው ። ይህ ስም ከጎሳ ቡድኑ ታሪካዊ አመጣጥ እና የቦታ ስፍረት ጋር ይዛመዳል። የብሔረሰቡ አዋቂ አባቶች በሙሉ በህዝቡ ታሪክ እና ባህል ላይ የሚስማሙበት አንድ ነጥብ አለ ። በሁሉም ጥናት በተካሄደባቸው አካባቢዎች እና ሽማግሌዎች ከሚናገሩት ጭምር "አርጎባ" የሚለው ስም “አረቦች ገቡ" ከሚለው አማርኛ ሐረግ የተወሰደው ነው ። በሌላ በኩል አርጎባ የሚለው ቃል የተፃፉ ሰነዶችን በምንመረምርበት ጊዜ የተለያዩ ትርጉሞች አሉት ።

በዚህ ረገድ በከሳቴ ብርሃን የአማርኛ መዝገበ-ቃላት የሚገኘውን ግቤት ስር አርጎባን ከተመለከትን ትርጉሙ በይፋት ወረዳ ሙስሊሞች የሚኖሩበት እንደ ሆነ እንገነዘባለን ። ከዚህ ትርጓሜ ሁለት መሠረታዊ ነጥቦችን እንረዳለን አንደኛው ፣ አርጎባ የቦታ ወይም የግዛት ስም ነው ፣ ሁለተኛው አርጎባ የተባሉ የእስልምና እምነት ተከታዮች የሰፈሩበት አካባቢ ነው ። የአርጎባን ህዝብ ታሪክ ፣ ባህል እና ቋንቋ ጥናት ካደረጉ ምሁራን መካከል አንዱ ቮልከር እስቲትስ (Volker Stitz) ነው። በ "የመሀል ኢትዮጵያ የምዕራብያውያኑ የይፋት አርጎባ" (The Argobba of western Yifat, central Ethiopia) በሚለው ጥናታዊ ስራው ላይ አርጎባ የሚለው ቃል አርጎብኛ የሚናገሩ ፣ እስልምናን የሚከተሉ እንዲሁም በእርሻ ፣ በሽመና ወይም በንግዱ የተሰማሩ ሰዎችን የሚያመለክቱ ሲሆን ሙስሊም ኦሮሞን እና የአፋር እረኞችን ወይም አርሶ አደሮች የሆኑትን ክርስቲያን አማራ የማያካትት መሆኑን ጽፈዋል።









**የሚገኙት የት ነው?**
በአዲሱ የአስተዳደር ክፍል መሠረት ህዝቡ በአማራ ፣ በአፋር ፣ በኦሮምያ እና በሐረሪ ክልሎች ተሰራጭቷል ።

**በአማራ ብሄራዊ ክልል**
አርጎባዎች በአርጎባ ወረዳ፣ በአሉ ወረዳ አውራጃዎች ስር ፤ በደቡብ ወሎ ዞን ፣ ፍተቆማ ፣ አረራንቸሮ ፣ ቾሚዬ ፣ መዲና እና አፍሶ በሚከተሉት መንደሮች ውስጥ ይገኛሉ ። በተመሳሳይ ክልል ኦሮምያ ክልል ውስጥ የሚኖሩት በሸንኬ ፣ በቶሌጎ ፣ በጂሌ እና ቲሙጋ ፣ አርቱማ ፣ በፍሪስ ፣ በኢዬ ጎላ ፣ በቼፋ ጎላ እና በደዌ ነው ። በሰሜን ሸዋ ዞን ውስጥ በሸዋ ሮቢት ፣ በጎዜ ብራሳገዜ ፣ ማፍድ እና በአልዩ አምባ መንደሮች ውስጥ ይኖራሉ ።

**አፋር ብሄራዊ ክልል**
አርጎባ ጋጨኔ በተባለው
ልዮ ዞን 3 አውራጃ ሱፍ አገር ፣ በአባ በላይ ፣ መጠቅለያ ፣ በታች መጠቅለያ ፣ ብሎ ፣ ቼሳ ፣ ደብረኮ ፣ ቆካ በወዜ ፣ በወርቅ አምባ ፣ በማኮ አምባ እና በጭኖ መንደሮች ውስጥ ይኖራሉ ። በፋንታሌ የሚኖሩት በአዋሽ እና መተሃራ ከተሞች ውስጥ ሲሆን በአሚባራ ወረዳ ውስጥ ደግሞ በመልካ ወረር ነው የሚኖሩት ።

**የኦሮምያ ብሔራዊ ክልል**
በሁለት ዞኖች እና በአራት ወረዳዎች ይኖራሉ ። በምስራቅ ሐረርጌ ዞን ውስጥ በፈዲስ ወረዳ በነዚህ መንደር ይገኛሉ። በጉረቄሬ ፣ በአፈይዘሮ ፣ ኢሳኮይ ፣ ኢሺዬ ፣ ገንዳ አደም ፣ አቴሮ ፣ ኡርዴ ፣ አዳሻ ፣ ቃሊያ ፣ አዳዲ ፣ ሻንኮ ፣ ኡምሬ ፣ ሀጂጎዳ፣ ቤሮፊፌ ፣ አሬዳ ፣ ገንዳጋራ ፣ ጉቱሽ ፣ ኑሬ ኬሊቼ ፣ አሬር ሀሜሮ ፣ ፌካቲ ፣ ሳዲኮ በርበሬ ፣ ሮሪሶ ፣ ከላድ ፣ ኩሉለት ፣ ቶዊኮ ፣ አደምራሬ ፣ አመርክሌ ፣ ቤርዳ ፣ አደምሃኮላ እና ኩማሽ ናቸው። በምእራብ ሀረርጌ ዞን በሚኤሶ ወረዳ ውስጥ የሚኖሩት በቦርደዴ ፣ በአሰቦት እና በሜኤሶ ከተሞች ናቸው። በጭሮ ወረዳ በለጋ አርባ ቀበሌ እና በቼልኳቃቃ መንደር ላይ ፍሬ ፣ ባሴ ፣ በአደሌ ፣ በጌዳባ ፣ በቦራዲያ ፣ በጬሮራ እና የአንቻር እና ጉርባ በበደይ ቡካቻ ወረዳ ላይ ይኖራሉ።

**የሀረሪ ብሔራዊ ክልል**
አርጎባ የሚኖረው በኮረሜ ፣ ኡመርዲን ፣ ሀሊሎ ፣ ኤሌዲ ፣ ወራራዋ ፣ አለላ ፣ አፈር ደባ እና ቃቂ በሚባሉ መንደሮች ውስጥ በሁንዳኔ ወረዳ ውስጥ ነው ። አርጎባ በተለያዩ ክልሎች በጂኦግራፊአዊ መስፋፋታቸው ምክንያት እንደአማራ ፣ አፋር ፣ ኦሮሞ እና የሐረሪ ሕዝቦች ጎረቤቶች ሆነው ይኖራሉ ። የአየር ንብረት እና ዕፅዋቱ የቆላ፣ ወይናና ደጋ ነው። በ 1984 በተደረገው ቆጠራ የአርጎባባ ህዝብ ብዛት 60,412 ነበር።
የጸሎት ርዕሶች
1. እግዚአብሔር ለዚህ ህዝብ ራሱን ይገልጥ ዘንድ
2. ትውልዳቸውን፣ ስራቸውን ህዝባቸውን ይባርክ ዘንድ
3. በዚያ ህዝብ መካከል ያሉ ጥቂት አማኞችን እንዲያጸና፣ ለወንጌል መልዕክተኛነት ድፍረት እንዲሆናቸው
4. ለዚህ ህዝብ የወንጌል መልዕክት ይዘው የሄዱ ሚሲዮናውያንን እንዲጎበኝ
5. ቤተክርስቲያን በዚህዝብ መካከል እንድትተከል እናም አንድትጸና እንጸልይ !!

ምንጭ፡- ጆሽዋ ፕሮጀክት
ትርጉም ፡- ኪሩቤል ጎበና
አርትኦት፡- አማኑኤል ወንድማገኝ